አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 219 ሚያዝያ 9 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ

ፎቶ፡- ገበያ ገብሬ

የምስራቅ አፍሪካ ወታደራዊ የመረጃ ተቋማት ሽብርተኝነትን ለመከላከል በትብብር እንደሚሠሩ ገለጹ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የምስራቅ አፍሪካ ወታደራዊ የመረጃ ተቋማት ሽብርተኝነትን ለመከላከልና የቀጣናውን ዘላቂ ሠላም ለማስጠበቅ በትብብር እንደሚሠሩ ገለጹ።

የምስራቅ አፍሪካ የመከላከያ ወታደራዊ መረጃ መድረክ በኢትዮጵያ አዘጋጅነት ትናንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመከላከያ ሠራዊት መረጃ ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጄነራል ብርሀኑ በቀለ፤ ምሥራቅ አፍሪካ የጸጥታና ደህንነት ሁኔታ አሸባሪዎች፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እንዲሁም ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር ያለበት መሆኑን ጠቅሰዋል። እነዚህ ሁሉ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የጸጥታና የደህንነት ስጋቶችን ለመከላከል አገራት በትብብር መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ቀጣናውን እየፈተኑ ያሉ እንደ አልሻባብ፣ አይ ኤስ

የምስራቅ አፍሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ከፋይል

“የአካባቢ ስያሜን መቀየር የኢትዮጵያን መቦጫጨቅ የሚፈልጉ አካላት የሚያሰራጩት የሐሰት ፕሮፖጋንዳ ነው”

- አምባሳደር ተፈራ ሻዎል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ሰሜን ጎንደርን ሌላ ስያሜ በማላበስ አንዱን ምዕራብ ሌላውን ምስራቅ ክፍል ነው የሚለው አገላለጽ የኢትዮጵያን መቦጫጨቅ የሚፈልጉ ሰዎችና ድርጅቶች የሚያሰራጩት የሐሰት ፕሮፖጋንዳ አካል መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባ አምባሳደር ተፈራ ሻዎል ገለጹ።

አምባሳደር ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ወልቃይትና ጠገዴ የሚገኙበት ሰሜን

“የአካባቢ ስያሜን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ቀይ መስቀል ማኅበር ለሰባት ሚሊዮን ዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ ማድረጉን አስታወቀ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት በሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ለችግር ለተዳረጉ ሰባት ሚሊዮን ዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ ማድረጉን የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር አስታወቀ።

የማኅበሩ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶክተር ሰለሞን አሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት፣ በድርቅና በሌሎችም ተያያዥ ችግሮች ምክንያት መጠነሰፊ ሰብዓዊ ቀውስ ተፈጥሯል። የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር በተያዘው በጀት ዓመት በሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ለችግር ለተዳረጉ ሰባት ሚሊዮን ዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ ማድረጉንና ከዚህ ውስጥ ሦስት ሚሊዮን የሚሆኑት በግጭትና ድርቅ ለችግር የተዳረጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በሚቀጥሉት ሰባት ወራትም ከአምስት መቶ ሺ እስከ ስድስት መቶ ሺ የሚደርሱ ሰዎችን ለማገዝ መታቀዱን ገልጸው፤ ለዚህ ደግሞ እስከ ሰባት መቶ ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል። ይህን ሀብት ለማሰባሰብም በዓለም አቀፉ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ በኩል ጥሪ የቀረበ ሲሆን በአገር ውስጥም ከበጎ አድራጊዎች የሀብት ማሰባሰብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ከግጭት፣ ድርቅና ሌሎችም ችግሮች ጋር በተገናኘ 20 ሚሊዮን የሚደርሱ ዜጎች ቀጥታ እርዳታና መልሶ ማቋቋም ይፈልጋሉ ያሉት ዶክተር ሰለሞን፤ ማኅበሩም በሚሰበስበው ሀብት መጠን ለተረጂዎች የዕለት ደራሽ እርዳታ ከማድረግ ባለፈ

ቀይመስቀል ማኅበር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ዶክተር ሰለሞን አሊ

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላቀ አገልግሎት ተሸላሚ ሆነ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅና አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በ2013/14 ዓ.ም ባስመዘገበው አፈፃፀም የላቀ አገልግሎት ተሸላሚ ሆነ፡፡

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር አሸናፊ ታዘበው እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሕክምና ማኅበር ሽልማቱን ማዘጋጀቱን አድንቀዋል።

ሽልማቱ ተቋሙ ለሠራቸው በርካታ ሥራዎች ዕውቅና የሚሰጥና ባለሙያዎችንም ለተሻለ ውጤት የሚያነቃቃ ነው ብለዋል፡፡

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅትም ሆነ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተከሰተው ጦርነት ላይ ከሕክምና ባለሙያዎቹ በተጨማሪ የአስተዳደር ሠራተኞችና የአካባቢው ወጣቶች እንዲሁም ከማኅበራት ጋር ተቀናጅቶ ሲሠራ እንደቆየ ገልፀዋል፡፡

እንደ ዶክተር አሸናፊ ገለፃ፤ ባለሙያዎች ወደ ጦርነት ሄደው ሙያዊ እገዛ እንዲሰጡ ከመደረጋቸው በፊት በሥነ ልቦና ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ ልዩ ሥልጠና ተሰጥቷል። ዝግጅቱም ጥሩ ውጤት ስለተገኘበት የሕክምና ባለሙያዎች ግንባር ድረስ ዘልቀው የሕክምና እርዳታ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

አስቀድመን ልዩ ዝግጅት በማድረጋችን በጦርነቱ ምክንያት በርካታ የሆኑ ቁስለኞች ወደ ሆስፒታሉ መጥተው ሕክምና አድርገውና ሙሉ ለሙሉ አገግመው መሄድ ችለዋል ብለዋል፡፡

ተቋሙ ለላቀ አገልግሎት ሽልማት የበቃው በአካባቢው ካሉ የጎንደር ከተማ ወጣቶች ጋር በትብብር በመሥራቱ ነው ያሉት ዶክተር አሸናፊ፤ በተለያዩ ወቅቶች በበጎ ፈቃደኝነት ሲያገለግሉ ለነበሩ ለአካባቢው ተወላጆችና የወጣቶች ማኅበራት ምሥጋና አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል ተቋሙ ለወደፊቱ በጦርነትም ሆነ የተለያዩ ወረርሽኞች ሊከሰቱ እንደሚችሉ በማሰብ ተፅዕኖውን ሊቋቋሙ የሚችሉ ሐኪሞችን ለማፍራት እንደሚሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከአለፉት ፈተናዎች አንጻር ተፅዕኖ ሊቋቋም የሚችል የጤና ባለሙያ ማፍራት እንዳለብን ተምረናል ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን በአጫጭር ሥልጠና ብቻ ሳይሆን በጤና የትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ተካተው እንዲሰጡ ለማስቻል ጥረት እያደረግን ነው ብለዋል፡፡

በተቋም ደረጃ ከዚህ በፊት የቀውስ ጊዜያት ተብለው በትኩረት ሲሠራባቸው ከነበሩ ጉዳዮች ባለፈ በመሆኑ በመጪው ጊዜ ለመደበኛ ሥራዎች ትኩረት በመስጠት መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን፤ በተደጋጋሚ ተሸላሚ ለመሆን እንሠራለን ሲሉ ተናግረዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በጦርነቱ የተነሳ ጉዳት የደረሰባቸውን ሆስፒታሎች መልሶ ለማቋቋም የተሠራው ሥራ ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመው፤ ዩኒቨርሲቲው ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ መድቦ የጤና ተቋማትን እየደገፈ መሆኑም ገልጸዋል።

ለተለያዩ ጉዳት ለደረሰባቸው የጤና ተቋማት የሕክምና ዕቃዎችንና መድኃኒቶችን ድጋፍ ማድረጉን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው በጤና ሳይንስ ኮሌጁና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሉ አማካኝነት የአስቸኳይ ጊዜና የአደጋዎች ዝግጁነት ማዕከላትን ማቋቋሙን ጠቁመው፤ ከፌዴራልና ከክልል መንግሥታት እንዲሁም ከከተሞች ጋር በመቀናጀት የሚሠራ የዝግጁነት ማዕከል ማዘጋጀቱን ሥራ አስፈፃሚው ተናግረዋል፡፡

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አየለ ተሾመ በበኩላቸው፤ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት ከወረርሽኝ ቅኝት ጀምሮ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ለደረሰ ልዩና የላቀ አገልግሎት እንዲሁም በጦርነት ወቅት ለሠሩት ተመሳሳይ ሥራ የጤናው ሴክተር

የሽልማት ሥነ ሥርዓቱ በተከናወነበት ወቅት

በመላ ምሥጋና እንደሚገባቸው ገልፀዋል፡፡

አያይዘውም በሁለተኛው የአምስት ዓመት የጤና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ አንዱና ዋነኛው የጤና ባለሙያዎችን ተነሳሽነት ለማሳደግ በትኩረት መሠራት እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መሠረት የጤና ባለሙያዎችን ተነሳሽነት ለመጨመር ከዚህ ቀደም የነበሩ የማትጊያ ሥርዓቶችን በመከለስ ሂደት ላይ እንገኛለን ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር አየለ ገለፃ፤ በሕክምና ማኅበሩ እንዲህ ዓይነት የማትጊያ ሽልማቶች መደረጋቸው የጤና ዘርፉን ለማነቃቃት አጋዥ እንደሆነና በዘርፉ ላይ አወንታዊ ለውጥ ለማምጣት ይረዳል፡፡ የጤና ሚኒስቴር እና የጤና ማኅበራት ቅንጅታዊ ሥራዎች የተሻለና ጥራት ያለው አገልግሎት ለማምጣት አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ሽልማቱን ያዘጋጀው የኢትዮጵያ ሕክምና ማኅበር በሙያቸው ለአገር የሚጠቅም ሥራ የሠሩ ግለሰቦችን፣ በጤናው ዘርፍ በዩኒቨርስቲዎች እየተማሩ ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችንና የአገልግሎት ጥራት ያስመዘገቡ ተቋማትን በየዓመቱ ይሸልማል፡፡

ማኅበሩ በኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰውን የውጭ ጫና በመሞገት ላበረከተው አስተዋጽዖ ምስጋና ተቸረው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር በኢትዮጵያ እየደረሰ ያለውን የውጭ ጫና በመሞገት ላበረከተው አስተዋጽዖ ከተለያዩ ተቋማት ምስጋና ተቸረው።

መንግስት በቀጣይም ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር ጋር በትብብር እንደሚሠራም ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር ትላንትና ለቀድሞ የማኅበሩ አመራሮቹና አጋር አካላት የዕውቅና መርሐ ግብር አካሂዷል። በወቅቱ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ እንደገለጹት፤ ማኅበሩ በኢትዮጵያ እየደረሰ ያለውን የውጭ ጫና በመሞገት ረገድ ሙያዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ የሙያ ማኅበር ነው፡፡

ማኅበሩ ምዕራባውያን ሐሰተኛ መረጃን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ላይ የከፈቱትን ጫና በመሞገት ረገድ ያበረከተው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለፃ፤ የማኅበሩ ሙያዊ ስነምግባርን የጠበቀ ሙግት ኢትዮጵያ በውጭው ዓለም የተከፈተባትን የተቀናጀ ዘመቻ በመቋቋም ሂደታ ውስጥ ሚናው የጎላ አለው፡፡

የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር የሚያወጣቸውን መግለጫዎችና የሰጣቸውን

ሰላማዊት ካሳ፤

ስልጠናዎች በቅርበት እንደሚከታተሉ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ መንግሥት በቀጣይም ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር ጋር በትብብር እንደሚሠራም ተናግረዋል።

በመርሐግብሩ የታደሙት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ

ፎቶ፡ በሳይ ኦስፋቸው

ዶክተር ዳንኤል በቀለ፤

መብቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማረጋገጥ ሂደት ላይ የመገናኛ ብዙኃን ሚና ከፍተኛ ነው። በዚህ ረገድ የማኅበሩ ጅምር ሥራዎች ሊበረታቱ ይገባቸዋል።

ዶክተር ዳንኤል እንደገለጹት የጋዜጠኝነት ሙያ ማኅበሩ በሰብዓዊ መብትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጋቸውን ጥረቶች አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል።

የሙያ ማኅበሩም በተደራጀ መንገድ የሚያከናውነውን ሥራ ለማገዝ ጥረት እናደርጋለን ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በቀጣይም ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር በጋራ የሚሠራቸው ሥራዎች ይኖሩታል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በሽግግር ላይ እንደምትገኝ የገለጹት ዶክተር ዳንኤል አገሪቷ የምትገኝበት ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶችም ለብዙኃን መገናኛዎች ፈተና እየሆነ እንደመጣ በመግለፅ ፈተናዎቹን በመቋቋም ዘርፉን ከዚህ በላይ ማሻገር ይገባል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማኅበር ከቀድሞ አመራሮቹ ለሆኑት ለጋዜጠኞች ኤልያስ መሠረት፣ ጋዜጠኛ ጎበዜ ሲሳይ፣ ጋዜጠኛ ደመቀ ከበደ፣ ጋዜጠኛ ሀብታሙ ደባሱ እንዲሁም ጋዜጠኛ ኤርምያስ በጋሻው ዕውቅና ሰጥቷል።

በተመሠረተ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በርካታ ተግባራትን ማከናወን የቻለው የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች ባደረጉለት ከፍተኛ ድጋፍና አስተዋጽዖ መሆኑን ያመለከተው ማህበሩ፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ ራይድ ዩኔስኮና መሰል ድርጅቶች በተለያዩ ጊዜያት ላደረጉት ትብብር ምስጋና አቅርቧል።

ርዕሰ አንቀፅ

የአገራዊ ትልሙ ስኬት የሁሉንም ትጋት ይጠይቃል!

አገራችን በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፋለች። በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት ተነሳች ሲባል እየወደቀች፤ አደገች ሲባል እየደቀቀች ዛሬም ድረስ ከርዳታና ብድር ሳትወጣ አለች። አጋርና ረጂ አካላትም አንዴ አለሁ ሲሉ ሌላ ጊዜ ጀርባ ሲሰጡ ፤ እርዳታና ብድርን ለእጅ መጠምዘዣነት ሲያውሉት አስተውለናል።

ለዚህ ሁሉ ዋናው ምክንያት አገራችን በተፈጥሮ የታደለች ሆና ይሄንኑ ዕድል እንደ ዕድል ሳንጠቀምበት በመቆየታችን ነው። በኢኮኖሚው፣ በማኅበራዊና በዴሞክራሲው የሚፈለገውን ለውጥና እድገት ማምጣት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ቢኖሩም ያንን በአግባቡ መጠቀምና መለወጥ ባለመቻላችንም ነው። ለበርካታ ጊዜያት መልካም አጋጣሚዎቻችንን ሳንጠቀምበት አጨናግፈናል። እናም ለማንም ለምንም ጥገኛ ላለመሆን ሚስጥሩ በሁሉም መልኩ ራስን መቻል ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው።

ለአገራዊ ክብር ሲባል በኢኮኖሚው ጡንቻን ማፈርጠም ወሳኝ ነው። ከውጪ ከማስገባት ለውጪ ገበያ አቅራቢ መሆን ፤በምግብ ሰብል ራስን መቻል፤ ከርዳታና ብድር መውጣት በአጠቃላይ የኢኮኖሚ አቅምን ማሳደግ አንዱና ወሳኙ ጉዳይ ነው። አገራችን ተፈጥሮ የባረካት ናት። ሰፊ የእርሻ መሬት ያላት፤ በቂ ውሀ የሚገኝባት፤ የተማረ ያልተማረው ሰፊ የሰው ጉልበት ባለቤት ናት። ይሄን ይዞ መራብ ፤ ይሄን ይዞ ለብድርና እርዳታ እጅን መዘርጋት በእርግጥም የሚያሳፍር ነው። በመሆኑም ያለንን መሬት ፣ ውሀ እና ጉልበት አስተባብረን ከድህነት መውጪያ የሆነውን የግብርና ሥራ ማጠናከር እና ኢኮኖሚያችንን በሚያጎለብቱ ዘርፎች ላይ መሠማራት አለብን።

አሁን በአገራችን የተጀመረው የቢጋ ስንዴ ፤ የቆላማ አካባቢ ልማት፣ የከተማ ግብርና በምግብ ራስን ከመቻል አልፎ ለውጪ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል መሆኑን ከተሞክሮው ለማየት ችለናል። ከረምት ጠብቆ አንዴ ያርስ የነበረውን አርሶ አደር በዓመት ሁለት ሶስት ጊዜ መስኖ በማልማት ተጠቃሚ መሆን ችሏል። ይሄንን የሚያጠናክር የአነስተኛ የመስኖ ግንባታ ሥራዎች በብዛት ተጀምሯል። ይሄ በገጠር አካባቢ ብቻም ሳይሆን በከተማ ውስጥም ውጤታማ መሆኑ በተጨባጭ ታይቷል።

የመንግሥት ራዕይና መንገድ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በቀጣዮቹ 10 ዓመታት ታላላቅ ኢኮኖሚ አላቸው ከሚባሉ የአፍሪካ አገራት ከግንባር ቀደሞቹ ተርታ ኢትዮጵያን ማሰለፍ ነው። እ.ኤ.አ. በ2050 ከዓለም ጠንካራ ኢኮኖሚ ካላቸው 20ዎቹ ውስጥ አገራችን መግባት አለባትም የሚል ነው። ትልሙንም ለማሳካት በቆራጥነት እየተሠራ ሲሆን ምቹ ዕድል አለ። ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊዮን የሚበልጥ የሰው ቁጥር አላት። ይሄንን የሰው ኃይል በአግባቡ መምራትና ማሠራት ከተቻለ በሁሉም ዘርፎች የታሰበው ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚቻል ይታመናል ።

አገራችን ከአስር ዓመት በኋላ በሁሉም መስክ ጠንክራ መውጣት አለባት። ከአፍሪካ ታላላቅ ኢኮኖሚ ካላቸው የመጀመሪያዎቹ ተርታ መሰለፍ፤ የምግብ ዋስትናዋን በማረጋገጥ ትልቅ አገር የማድረግ ራዕይ በመንግሥት ተይዞ ወደ ሥራ ተገብቷል። ይሄንን ራዕይ ለማሳካት ታዲያ የሁሉንም ትጋት ይጠይቃል። በሁሉም መስክ የታለመውን ማሳካት የሚቻለው ሁሉም ተባብሮ መሥራት ሲቻል ነው። በአገራችን በቂ የሆነ አቅም አለ ፤ ስለሆነም በሁሉም መስክ እድገትና ለውጡ እንዳይቆም በየደረጃው መጠንከር ያስፈልጋል።

አገራዊ ትልሙ ህልም ሳይሆን ሊሳካ የሚችል እቅድ ነው። ይሄንን ማሳካት የሚቻለው ታዲያ በአገሪቱ ያለውን ሀብት አውቆ ያንን አቀናጅቶ የሚመራ ብቁ መሪ በየደረጃው ሲኖር፤ ሕዝቡም ለእኔ ነው ፤ለአገሬ ነው ብሎ መሥራትና ትልሙን ለማሳካት ሲተጋ ብቻ ነው።

ዕድገት የሁሉንም ትብብር ይሻልና መንግሥት ስለፈለገ ብቻ የሚመጣ ዕድገትና ብልጽግና አይኖርም። ወደኋላ የሚጎትቱትን ሳይሆን ወደፊት የሚያስፈነጥሩ አስተሳሰቦችን አንግቦ መጓዝንም ይጠይቃል። ያደጉ አገራት ብለን የምንቀናባቸው ፤ እጃችንን ዘርግተን እርዱን አበድሩን የምንላቸው አገራት ያደጉትና ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ የደረሱት መና ከሰማይ ወርዶላቸው አይደለም። እጃቸውን አጣጥፈው በመቀመጥም አይደለም። ከችግር ተምረው መሥራት እንደሚለውጥ አምነውና ሳይታክቱ ሠርተው እንጂ። ለማደግ መክፈል የሚገባቸውን መሰዋዕትነት ከፍለውም ነው።

እኛም ትልማችንን ለማሳካት ካንቀላፋንበት መውጣትና መሥራት አለብን። ሠርተን መለወጥ ይጠበቅብናል። ተረጂ ሳይሆን ረጂ፣ ሸማች ሳይሆን ለውጪ አቅራቢ መሆን ይገባናል ። አሁን ያሰብነውን ማሳካት የሚያስችለን ሀብት በእጃችን አለን። ያለንን ሀብት ወደ ምርታማነት መቀየር ነው የሚጠበቅብን። ለዚህ ደግሞ በቅድሚያ ራሳችንን ከስንፍናና ከአጉል አስተሳሰብ ማራቅ አለብን። ለማደግና ከተረጂነት ለመውጣት መወሰን ፤ ያሰብነውን ትልም ለማሳካትም ተባብረንና ጠንክረን መሥራትም ይገባል!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

የግለሰቦችን ብልህነት የሚጠይቀው የኑሮ ውድነት

መሳኩ ኤሮሴ

ከእለት ወደ እለት እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት አሳሳቢ ሆኖ ቀጥሏል ፡፡ የምግብ እህል ፣ የቤት ኪራይ ፣ የነዳጅ ፣ የሸቀጣሸቀጥ ፣ ማዳበሪያ፣ የዘር እህል ወዘተ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመምጣቱ አብዛኛው ሕዝብ የእለት ጉርሱን ፤ የዓመት ልብሱን፤ አንገት ማስገቢያ ጎጆ እንዲያገኝ እያደረገው ይገኛል፡፡ በአገራችን የኑሮ ውድነት እንዲባባስ ምክንያት እየሆነ ነው ተብሎ በተለያዩ አካላት የተለያዩ ምክንያቶች ሲጠቀሱ ይስተዋላል ፡፡ በአንድ በኩል የንግዱ ማኅበረሰብ የሚፈጥራቸው ችግሮች ዋነኛው መንስኤ እንደሆነ ሲነሳ በሌላ በኩል አገሪቱ የገባችበት ጦርነት ያስከተላቸው ኢኮኖሚያዊ መዘዞች ችግሩ እንዲባባስ ስለማድረጉ ይነሳል ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ የአገሪቱ የግብርና ዘርፍ አለመዘመን የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወጣ ሲያነሱ አንዳንዶቹ ደግሞ የአገሪቱ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግሮች የፈጠሩት እንደሆነ ያነሳሉ ፡፡ በሌላ በኩል ከላይ የተዘረዘሩ ምክንያቶች ድምር ውጤት ነው ይላሉ ፡፡

የኑሮ ውድነት መንስኤዎች ናቸው ተብለው በተለያዩ አካላት የሚጠቀሱ ምክንያቶች እንደሚለያይ ሁሉ እንደመፍትሔ የሚጠቀሱትም ይለያያል። አንዳንዶች ምርትና ምርታማነትን ማሳደግን እንደመፍትሔ ሲያነሱ ፣ ሌሎቹ የንግዱን ማኅበረሰብ አደብ ማስገዛትን እንደ ዋነኛው መፍትሔ ይጠቅሳሉ። ሌሎቹ ጦርነቱን በሰላማዊ መንገድ መቋጨትን እንደመፍትሔ ያነሳሉ ፡፡ በአጠቃላይ እንደ ምክንያትና መፍትሔ የሚጠቀሱ ነገሮች ከመንግሥትና ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር የሚገናኙ ናቸው ማለት ይቻላል ፡፡

በዚህ ሁሉ መሐል አንድ ቁልፍ መፍትሔ የተዘነጋ ይመስላል ፡፡ የትኛውም ጥረት ግብ ሊመታ የሚችለው የሕዝብ ተሳትፎና ባለቤትነት ሲታከልበት ነው፡፡ በአገራችን የብዙዎች ራስ ምታት የሆነውን የኑሮ ውድነት ለመቋቋም ግለሰቦችና ቤተሰቦች የሚወስዷቸው የመፍትሔ እርምጃዎች ትልቅ ሚና እንዳላቸው ሊዘነጋ አይገባም ፡፡ የችግሩ መፍትሔ በመንግሥት እጅ ብቻ እንዳለ ማሰብ ችግሩን ለመፍታት አያስችልም ፡፡ መንግሥት ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር እያንዳንዱ ግለሰብ ወጪ መቀነሻ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል ፡፡

የዜጎች የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል የማድረግ ዋነኛ ኃላፊነት የመንግሥት ቢሆንም በአገራችን ውስጥ አሁን ከሚታየው የኑሮ ውድነት ከባድነት ለመላቀቅ ዜጎች የኑሮ ውድነት እያስከተለ ያለውን ጫና ለመቋቋም መፍረድ አይገባም ፡፡

የራስን ሸመታን በፕሮግራም እና በዝርዝር ማከናወን ሌላኛው መፍትሔ ነው ፡፡ ሰዎች ገበያ ከወጡ በኋላ ሳይሆን ከመውጣታቸው በፊት ስለሚሸምቱት ነገር እና መጠን መወሰን ፤ ካሰቡት የሸመታ ፍላጎት በላይ በጀት ይዞ ወደ ገበያ ያለመውጣት በጣም ተገቢ ነው ፡፡ ካሰቡት የሸመታ ፍላጎት በላይ ገንዘብ ይዘው የሚወጡ ከሆነ ያላሰቡትን ምርትና አገልግሎት የመሸመት እድል ይሰፋል ፡፡ ይህንን ችግር ለመከላከል መፍትሔው የተመጠነ በጀት ይዘው መውጣት ነው፡፡

የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም ሌላኛው መፍትሔ ማተካካት ነው ፡፡ ዋጋው ከፍ ያለውን ምርት በመተው ዋጋው ተመጣጣኝ ነገር ግን ዋጋው ከፍ ካለው ምርት ጋር ተቀራራቢ ጥቅም ሊሰጥ የሚችል ምርት መሸመትን መልመድ ያስፈልጋል ፡፡ ለአብነት ያህል አንድ ሸማች ምስር ሊገዛ ወጥቶ የምስር ዋጋ ካሰበው በላይ ከፍ ብሎ ካገኘ እና የሽሮ ዋጋ መጠነኛ ቅናሽ የሚታይበት ከሆነ ምስርን በሽሮ መተካት የኑሮ ውድነትን በጊዜያዊነት ለመቋቋም ይረዳል፡፡

ከገቢ አንጻር ሰዎች የሚጠቀሟቸውን ምርቶችና አገልግሎቶችን ተመጣጣኝ ወጪ በሚያስወጡ ምርቶችና አገልግሎቶች መተካት የኑሮ ውድነት ለመቋቋም ሚናው ከፍ ያለ መሆኑን የምጣኔ ሀብት ሊህቃን ያስረዳሉ ፡፡

ብድር የወጪ ሁኔታን የማዛነፍ አቅም እንዳለው የዘርፉ ምሑራን የሚያስረዱ ሲሆን ፤ ወደፊት የሚኖር የወጪ ምክንያት እንዳይጨምር ከብድር ራስን ማራቅ፡፡ የነበረ ብድር ካለ በፍጥነት በተቻለ አቅም ከፍሎ ከእዳ መላቀቅ የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም ሚናው የላቀ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል ፡፡

የተሻለ ዋጋ ያላቸው ገበያዎችን መርጦ መሸመት ሸማቾችን ከአላስፈጊ የዋጋ ጭማሪ የሚከላከል በመሆኑ፤ የገበያ ዋጋ ጥናት ቀድሞ በማድረግ ምርቶችና አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ከሚሸጥባቸው አካባቢዎች መሸመት የራሱ ሚና አለው ፡፡ በአጠቃላይ ግን ሸማች የኑሮ ውድነትን ለመከላከል አንዱ የመፍትሔው አካል መሆን እንደሚችል ማመን አለበት። ወጪ ቀናሽ ምርቶች ላይ ማተኮር፤ አማራጭ ምርቶች ላይ ማተኮር፣ ባለመግዛት አድማ ማድረግ በመፍትሔነት የሚያገለግሉ መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። ለእያንዳንዱ ችግር ሁሉም በራሱ መላ ቢፈልግለት ችግሩን በመጠኑም ቢሆን ሊቀንስ ይችላል። ሁልጊዜም መንግሥትን ብቻ ከመጠበቅ በራስም የመፍትሔ አካል መሆን ተገቢ ነው።

በአገራችን ለምርቶች ዋጋ መናር እና ከገበያ መጥፋት አንዱ ምክንያት እየሆነ ያለው የንግዱ ማኅበረሰብ እንዲሁም ሸማቾች የእቃዎች ወይም የምርቶች ዋጋ በቀጣይ ጊዜያት ሲጨምር ይችላል በሚል ስጋት ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ገዝቶ ማከማቸት ነው

በፕሮግራም መኖርና በፕሮግራም መሸመት እጅግ ወሳኝነት አለው ፡፡ በፕሮግራም የማይሸምት ሸማች ገበያ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይቸገራል ፡፡ ያለ እቅድ ገበያ በወጣ ቁጥር የሚያምር እቃ ሲያገኝ ወይም ሰዎች በብዛት የሚገዙትን እቃ ሲያገኝ የሚገዛ ሸማች የኑሮ ውድነት ጫናን ለመቋቋም ይቸገራል ፡፡

በአገራችን ለምርቶች ዋጋ መናር እና ከገበያ መጥፋት አንዱ ምክንያት እየሆነ ያለው የንግዱ ማኅበረሰብ እንዲሁም ሸማቾች የእቃዎች ወይም የምርቶች ዋጋ በቀጣይ ጊዜያት ሊጨምር ይችላል በሚል ስጋት ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ገዝቶ ማከማቸት ነው ፡፡ ሸማቾች ባልተረጋገጠ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ምርቶችን በማከማቸት ለዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት መባባስ ምክንያት ሊሆኑ አይገባም ፡፡ አንድ ሸማቾች ለወራት የሚሆን ምርት በሚሰበስቡበት ወቅት በገበያ ውስጥ የምርት እጥረት ስለሚያጋጥም ወቅት ለዕለት የሚሆን ምርትና ሸቀጥ የሚፈልጉ ሸማቾች ችግር ውስጥ ሊወድቁ እንደሚችሉ ከግምት ማስገባት አለባቸው ፡፡ የወር የመግዛት አቅም የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ችግር ውስጥ እንዲወድቁ

ዜና

በ705 ሺህ ሕግን በተላለፉ አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ መውሰዱን ኤጀንሲው ገለጸ

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት በ705 ሺህ ሕግን በተላለፉ አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ መውሰዱን የአዲስ አበባ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ገለጸ፡፡ ኤጀንሲው አዲስ የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎችን የደንብ ልብስ ይፋ አደረገ፡፡

የኤጀንሲውን ያለፉት ዘጠኝ ወራት የሥራ እንቅስቃሴ አስመልክቶ መግለጫ የሰጡት ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ክበበው ሚደቅሳ እንደገለጹት፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 705 ሺህ ሕግን ተላልፈው በተገኙ አሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል፡፡

በግንዛቤ የተደገፈ ጥብቅ የትራፊክ ቁጥጥር በማድረግ በትራፊክ ግጭት አደጋ የሚያደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስና ለማስቀረት ተሠርቷል።

ያጋጠሙ ችግሮችን በሚቀጥሉት ሶስት ወራት ለመፍታት እንደሚሠራም ዋና ዳይሬክተሩ አመልክተዋል።

በሌላ በኩል ኤጀንሲው አዲስ የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎችን የደንብ ልብስ ይፋ አደርጓል፡፡ ኤጀንሲው ይፋ ያደረገው የትራፊክ ቁጥጥር የደንብ ልብስ የቁጥጥር ስራውን ለማጠናከርና የተመሣሣይ አንፀባራቂ ልብስ በመልበስ የተሽከርካሪ ዘረፋና ሌብነት ተግባርን ለመቅረፍ የሚያግዝ ነው ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የኤጀንሲው የቁጥጥር ባለሙያዎች እና የሚያከናውናቸው ተግባራት በከተማዋ በተለይ ሰሞኑን እየተስተዋለ የሚገኘው በአንድ ጊዜ የበርካታ ዜጎችን ሕይወት እየቀጠፈ የሚገኘውን አደጋ ለመቀነስ እና ለማስቀረት ነው።

ፎቶ፡- ሀዲሽ አብርሐ

ኤጀንሲው ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ትራፊክ ፖሊሶች ጭምር የሚሆኑ ጠጥቶ ማሽከርከርን ለመቆጣጠር የሚረዱ 100 ሺህ የትንፋሽ መፈተሻ እና 10 የአልኮል መጠጥ መመርመሪያ መሣሪያዎች፣ የፍጥነት መቆጣጠሪያ ራዳሮች፣ የትራፊክ ግጭት አደጋዎች ወቅት የሚያገለግሉ ኮኖች፣ ቾክ እና የመሳሰሉትንም እያሟላ መሆኑን ተናግረዋል።

የኤጀንሲው የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች የትራፊክ ማስተናበርን ጭምር በንድፈ ሀሳብ እና በተግባር የተደገፈ ስልጠና ወስደው አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ናቸው ብለዋል።

ከፊታችን በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት በሚከበረው ፋሲካ በዓል ወቅት ከፍተኛ የትራፊክና የሕዝብ እንቅስቃሴ እንደሚኖር ታሳቢ ያደረገ በአሽከርካሪውና እግረኛው በኩል ተገቢ ጥንቃቄ እንዲደረግም አሳስበዋል።

የብዙኃን ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች የትራፊክ ሕግን እና ደንብን አክብረው እንዲያሽከረክሩ፣ እግረኞችም ተገቢውን የመንገድ ደህንነት ጥንቃቄ በማድረግ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ኅብረተሰቡን በማስተማር እና አስፈላጊ መረጃዎችን ወደ ሕዝብ በማድረስ ከኤጀንሲው ጋር በትብብር እንዲሠሩም ጥሪ አቅርበዋል።

የብሉምበርግ ኢኒሺየቲቭ የመንገድ ደህንነት የዳታ ምርመራ ባለሙያ ወይዘሮ ሜሮን ጌታቸው በበኩላቸው በወቅቱ እንዳሉት፤ ከሐምሌ 2013 ዓ.ም እስከ ታኅሳስ 2014 ዓ.ም ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ ከ2013 ዓ.ም የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት አንጻር የትራፊክ ሞት አደጋ በአምስት በመቶ የአካል ጉዳት ደግሞ በአስር በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

በከተማዋ ከአምስት የትራፊክ አደጋ ሞት ውስጥ አራቱ የሚደርሰው በእግረኞች ላይ ሲሆን ባለፉት ዓመታትም በተመሳሳይ የታየ መሆኑን ገልጸዋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታት በትራፊክ አደጋ በአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ ሞት ያስተናገደው ኃይሌ ጋርመንት አካባቢ ሲሆን ቦሌ ሚካኤል ደግሞ በሁለተኛነት ተቀምጧል።

የምስራቅ አፍሪካ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አይ ኤስና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሽብርተኞችን በተናጠል መመከት አስቻጋሪ መሆኑን ጠቁመው፤ ችግሩን ለመፍታት አገራት በጋራ መሥራት እንዳለባቸው የመምሪያው ኃላፊው ገልጸዋል።

በተጨማሪም በአገር ውስጥ እንደ ሸኔና ሕወሓት ያሉ አሸባሪ ቡድኖች የሕዝቡን ደህንነት አደጋ ላይ በመጣል ያደረሱትን በደል አስታውሰዋል። መሰል ጥቃቶችን አገራት መረጃ በመለዋወጥ መከላከል እንዳለባቸውም ነው ያስገነዘቡት።

እንደ ሌተናል ጄኔራሉ ገለጻ፤ በግሎባላይዜሽን ዘመን አንድ አካባቢ ያለው መልካም አጋጣሚም ሆነ ስጋት በአንድ አካባቢ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ለዚህም ከመልካም ነገር ልምድ በመውሰድ የበለጠ ማዳበር፤ መጥፎ ነገር ሲኖር ደግሞ ቀደም ብሎ መከላከል እንዲቻል የተዘጋጀው ፎረም አጋዥ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ፎረሙ ትብብር ለመፍጠር ልምድ ለመለዋወጥ በቀጣይነትም በትስስር መንፈስ ለየአገራቱ የደህንነትና የጸጥታ ስጋት የሆኑ ሁኔታዎችን ቀድሞ በማወቅና ቀድሞ ለመከላከል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እንደተዘጋጀም አንስተዋል።

ከዚህ ባለፈም ፎረሙ ለፖሊሲ አውጭዎች ተዓማኒ የሆነ መረጃን ለማቀበልና በመከላከያ ደረጃ ለመሥራት የሚያስችል ምቹ ውሳኔ ለመፍጠርም ይረዳል ነው ያሉት።

የጅቡቲ መከላከያ ኃይል መረጃ ኃላፊ ኮሎኔል ሜጀር አደን ዱአሌ በኢትዮጵያ ጋባዥነት በፎረሙ በመሳተፋቸው አመስግነዋል። ፎረሙ ጠንከር ያሉ ሀሳቦችን ለማንሳትና በየአገራቱ መካከል ያለውን ልምድ ለመጋራት ትልቅ እድል እንደሆነም ጠቅሰዋል።

የመረጃ ክፍል ለአገራቱ ደህንነት የጀርባ አጥንት እንደሆነ የጠቆሙት ኃላፊው፤ ያለመረጃ ልውውጥ ውጤታማ የደህንነት ሥራ ማከናወን እንደማይቻልና አሸባሪዎችን መመከት አዳጋች እንደሚሆን ገልጸዋል። የምስራቅ አፍሪካ አገራት ሽብርተኝነትን ለመከላከል ትብብርን ማዕከል ያደረገ ሥራ መሥራት ይኖርባቸዋልም ብለዋል።

ጅቡቲና ኢትዮጵያ በደህንነት ሥራዎች ጠንካራ ግንኙነት ያላቸው አገራት እንደሆኑና፤ ግንኙነቱን በወታደራዊ የመረጃ ልውውጥ ደረጃ ለማሳደግ ጅቡቲ ቁርጠኛ እንደሆነች ተናግረዋል። ጅቡቲ የተለያዩ አገራት የጦር ቤዝ መቀመጫ እንደመሆኗ ለምሥራቅ አፍሪካ አገራት ወታደራዊ መረጃዎችን ለመስጠት ቁርጠኛ ናት ሲሉም ገልጸዋል።

በምሥራቅ አፍሪካ አገራት የደህንነት መዋቅርና ትስስር መፍጠር ካልተቻለ አስቸጋሪ እንደሆነ የጠቆሙት ኃላፊው፤ ያለ መረጃ ልውውጥ ምንም ነገር ማከናወን የማይቻል በመሆኑ ጠንካራ ግንኙንትን በመፍጠር በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

የሶማሊያ መከላከያ ወታደራዊ ደህንነት ዳይሬክተር ሜጀር ጄነራል ሰአድ ሙሐመድ በበኩላቸው፤ የጋራ የደህንነት ፍላጎት ላይ ያተኮረው አጀንዳ ለአገራቱ መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ጠቅሰዋል። በቀጣናው ያሉ ሕዝቦች የባህል፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋና መሰል እሴቶችን እንደሚጋሩ ሁሉ፤ የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ሽብርተኝነትን በጋራ መከላከል እንዳለባቸውም አስታውቀዋል።

በፎረሙ ኢትዮጵያን ጨምሮ የኡጋንዳ፣ የኬንያ፣ የታንዛኒያ፣ የሱዳን፣ የደቡብ ሱዳን፣ የሶማሊያና ጅቡቲ አገራት የወታደራዊ መረጃ ኃላፊዎችና አታሼዎች ተሳትፈዋል።

ቀይ መስቀል ማኅበር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለመልሶ ማቋቋምና አስፈላጊ የልማት ሥራዎች ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል ብለዋል።

ማኅበሩ በአማራ፣ በአፋርና በሌሎችም ክልሎች በጦርነት፣ በድርቅና በሌሎችም ችግሮች ተፈናቅለው በመጠለያ ጣቢያዎች ለሚገኙ ዜጎች አስፈላጊ እርዳታዎች እንደሚያከናውን ጠቁመው፤ በቅርቡ የቀይ መስቀል አውሮፕላኖችንና ተሽከርካ ሪዎችን በመጠቀም የመድኃኒት፣ የምግብና ሌሎችም አስፈላጊ ቁሶችን ወደ ትግራይ ክልል እንደሚልኩም ተናግረዋል።

ማኅበሩ ትግራይ ክልል ውስጥ አራት መቶ ሠራተኞች እና ከአንድ ሺ በላይ በጎ ፈቃደኞች እንዳሉት አስታውሰው፤ እነዚህን መዋቅሮች በመጠቀም የሚላኩ እርዳታዎች ለተረጂዎች በአግባቡ እንዲደርሱ ጥረት ያደርጋል። ከሕዝቡ ጥሩ ምላሽ እየተገኘ ቢሆን ካለው ዘርፈ ብዙ ችግር አንጻር አሁንም መተጋገዝና መረዳዳትን ማጠናከር እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በትግራይ ክልል 20 ሺ ለሚሆኑ አባወራዎች የገንዘብና ምርጥ ዘር እርዳታ በማድረግ ወደ ምርት እንዲገቡ ለማገዝ ጥረት እያደረገ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር አቅሙን አሟጦ በተለያዩ መልኩ ችግር ላይ የተዳረጉ በርካታ ወገኖችን እየደገፈ መሆኑን ገልጸው፤ ማኅበሩ ለተቸገሩ ወገኖች የሚደርሰው ባለው ሀብት መጠን በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በ9400 አጭር የጽሑፍ መልዕክት፣ በማኅበሩ ቢሮዎችና በሌሎችም አማራጮች በአይነትና በጥሬ ገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር በመላው አገሪቱ 180 የሚሆኑ ቅርንጫፎች፣ 200 ሺ ሠራተኞችና ከ45 ሺ በላይ በጎ ፈቃደኞች እንዳሉት ከማኅበሩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

“የአካባቢ ስያሜን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጎንደር የኢትዮጵያ ክፍል ነው። ስሙን እየለወጡ ሌላ ስያሜ መስጠት ተገቢነት የለውም። ድርጊቱ ምዕራባውያን የሚያካሂዱት የተለመደ የሐሰት ፕሮፖጋንዳ አካል መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ተቋሙ አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዩማን ራይትስ ዎች ሰሞኑን በጋራ በመሆን በኢትዮጵያ ጉዳይ ሪፖርት ማውጣታቸው ይታወሳል።

እነዚህ ተቋማት የሰሜን ጎንደርን ስያሜ በመቀየር ሌላ ስም መስጠታቸው ተገቢነት የለውም ብለዋል። ሰሜን ጎንደርን ቀደም ሲል ወርረው ይዘውት፣ ስሙንም ለውጠው፣ በካርታም አቀማመጡን አበላሽተው ቆይተዋል ሲሉም አስታውሰዋል።

አሁን ደግሞ አካባቢውን በሪፖርት ሌላ ስያሜ ማላበስ ትክክል አይደለም። አንዱ ምዕራብ ሌላውን ምስራቅ ክፍል ነው በማለት የሚያሰራጩት የሐሰት ፕሮፖጋንዳ የኢትዮጵያን መቦጫጨቅ የሚፈልጉ አካላት የሚያወሩት የሐሰት ወሬ መሆኑን በመገንዘብ ትክክለኛውን ገጽታ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲገነዘበው ማድረግ ይገባል ብለዋል።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ ምዕራባውያን የውሸት ድርሰት በደህንነት ክፍላቸው አማካኝነት በመፍጠር የሐሰት መረጃ በማሰራጨት ሕዝብን የማሸበር እና የማደናር ተግባር የተለመደ ነው። ኅብረተሰቡ የሰሞኑ መረጃ የምዕራባውያን የፈጠራ ድርሰት መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል። በእንዲህ አይነት የሐሰት ፕሮፖጋንዳም መታለል የለበትም።

ምዕራባውያን ለማሸበር እና ለማደናበር የሚጠቀሙበት አንድ ዘዴ ሐሰተኛ መረጃ ነው። ኅብረተሰቡ በዚህ ድርጊት መሸበር አይገባውም ያሉት አምባሳደር ተፈራ፤ መንግሥት ከውሳኔ በፊት፤ ሕዝብም ከሆደ ባሻነት ይልቅ ቆም ብሎ ተረጋግቶ ማሰብ ይኖርባቸዋል። በሐሰት መረጃ መሸበር እጅ እንደመስጠት ይቆጠራል ብለዋል።

መረጃውን የሚያሰራጩትንም ለምን አሉ? ማለት ሳይሆን፤ ለሚያሰራጩት የሐሰት ፕሮፖጋንዳ ትክክለኛውን ገጽታ አለም አቀፉ ማኅበረሰቡ እንዲገነዘበው መሠራት አለበት፤ በተግባር ምላሽ መስጠት እንደሚገባም አመልክተዋል።

ዲፕሎማቶች በዚህ ተግባር ባግባቡ ሊሠሩ እንደሚገባ የጠቆሙት አምባሳደር ተፈራ፤ በጋዜጦች፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ፣ በተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም፤ በእንግሊዝኛ፣ በአረብኛ፣ በፈረንሳይኛና በሌሎች ቋንቋዎች ጭምር በሚሠሩ ፕሮግራሞች ማጋለጥ ይገባል፣ እውነታውን ለማሳወቅ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ቢቢሲ እስከትግራይ በማለት የሚያራምደው አቋም አለ፣ ተቋሙ ኢትዮጵያን ሁል ጊዜ የመገዳደር ተግባሩ አካል ነው። ጥሩ ሥራ ሲሠራ አይዘግቡም፣ ወደ ትግራይ የሚጓጓዘው ምግብ መንገድ ላይ በማን እንደተገታ እንኳን እውነታውን እንዳልዘገቡም ነው የጠቆሙት።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

ነፃ ሃሳብ

በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቀምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

የሚገባውን ትኩረት የተነፈገው የጎንደር ዩኒቨርሲቲ አስደንጋጭ ግኝት ...!?

(የመጨረሻ ክፍል - ከዓርብ እትም የቀጠለ)

በዚሁ ሳምንት በእለተ ሐሙስ እና ዓርብ እትሞች በተከታታይ ባስነበብኋቸው መጣጥፎች፤ ሰሞነኛውና አስደንጋጩ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የጥናት ግኝት ላይ ተመርኩዤ ሕወሓት በዘር ማጥፋት ጥርሱን የነቀለ ወንጀለኛ የሽብር ቡድን ቢሆንም ይሄን ማንነቱን በልኩ ባለማጋለጣችንና ባለማሳወቃችን እውነትን ታቅፈን መቅረታችንና በዲፕሎማሲውም ሆነ በሚዲያው ብልጫ እንደተወሰደብን በቁጭት ገልጬ ነበር። በዛሬው የመጨረሻ ክፍል መጣጥፌም ካቆምሁበት የምቀጥል ሆኖ፤ ከዚያ በፊት ግን ሰሞኑን የዓለም የጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሀኖም ድፍረት የተሞላበት፣ አስደንጋጭና ተስፋ መቁረጥ የተንጸባረቀበት ክስ አይሉት ፍረጃ ምዕራባውያን ላይ ደርቷል። ምዕራባውያን ለዩክሬን የሰጡትን ትኩረት ያህል ለትግራይ ያልሰጡት ዘረኞች ስለሆኑ ነው ማለቱን “ዘ-ጋርዲያን” ዘግቧል።

ምዕራባውያን ለቆዳቸውና ለስጋቸው እንደሚያደሉ ሳይታለም የተፈታ ጥሬ ሀቅ ነው። ዘረኝነትን በገዛ ዜጎቻቸው ሳይቀር እንደሚያራምዱ ጸሐይ የሞቀው የአደባባይ እውነት ነው። ይሄን ራሳቸውም ያምናሉ። ጆ ባይደን በዚያ ሰሞን ዘረኝነት በአሜሪካ ተቋማዊ መሆኑን ያለምንም ማቅማማት ተናግረዋል። እጁ በዘረኝነት ደም የጨቀየው ሕወሓት፣ ከሳሽ ሆኖ ሲመጣ ግን ጋዜጠኛ ሔርሜላ ሰሞኑን በቲዊተር ገጿ እንዳለችው ምጸት፣ ልግጫና ሾርኔ ይሆናል።

የጥቁሩ አፓርታይድ ሕወሓት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነው ዶ/ር ቴዎድሮስ ግን ስለ ዘረኝነት የማውራት ምንም አይነት የቅስም ልዕልና የለውም። አገዛዝ ላይ ለመቆየት አገራችንን በዘር ከፋፍሎ ሲያባላ የኖረ፤ የማንነት፣ የጥላቻና የልዩነት ፖለቲካ ሲነነቁል የኖረ፤ አንድን ብሔር በጠላትነት ፈርጆ ዘር ሲያጠፋና ሲያጸዳ የኖረ፤ እኩልነትን እንደ ሀጢያትና ወንጀል ቆጥሮ አገራችንን ለማፍረስ ሲኦልም ቢሆን እወርዳለሁ ያለ ዘረኛና ጠባብ ብሔርተኛ ፓርቲ አራጊ ፈጣሪ የሆነ ወንጀለኛ አይደለም ምዕራባውያንን ዲያብሎስን፣ ሒትለርንና ሞሶሎኒን በዘረኝነት የመክሰስ የሞራል ልዕልና የለውም።

ለዚህ ሁሉ ያበቃነው ግን እኛ ራሳችን ነን። በአገሪቱ ስምና ሀብት ለስልጣን አብቅተነው የአሸባሪው ሕወሓት “የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤” ሆኖ ሲያርፈው፤ ኃላፊነቱንና የድርጅቱን ሀብት ለሕወሓት ድጋፍ ማሰባሰቢያ ሲያደርገው፤ ስልጣኑን ሽፋን አድርጎ በሀሰተኛ ክስ ከምዕራባውያን ሚዲያዎችና ከእነ አመነስቲ ጋር አብሮ ቁምስቅላችንን ሲያሳየን ባላየ ባልሰማ አለፍነው። ሌላው ይቅርና ከሁለት ወይም ሶስት ወራት በፊት የጥቅም ግጭት ስላለበትና ገለልተኛም ስላልሆነ እንዲጣራ ለድርጅቱ ቦርድ ያቀረብነው መናኛ አቤቱታ እንኳ ከምን እንደደረሰ ተከታትለን አልጠየቅንም። ኢጋድንና የአፍሪካ ሕብረትን አስተባብረን ከእኩይ ተግባሩ እንዲታቀብ ግፊት ማድረግ፤ ከፍ ሲልም ከኃላፊነት እንዲነሳ አልቀሰቀስንም ። ለኤች.አር6600 እና ኤስ3199 የዳረገንም ይሄ እንዝህላልነትና ዳተኝነት ነው ።

የዓለም የጤና ድርጅት በጤና ተቋማት ላይ የሚፈጸም ጥቃት የቅኝት ስርዓት/Surveillance system for attacks on health care /(SSA) አለው። ለዚሁ በተዘጋጀ መተግበሪያ እኤአ ከ2018 እስከ 2020 ዓ.ም በመላው ዓለም 2ሺህ 119 ጤና ተቋማት ጥቃት መሰንዘሩን ገልጿል። በዩክሬን በጤና ተቋማት ላይ ስለተፈጸመ ጥቃት በዚህ የመረጃ ቋቱ ከመመዝገብ አልፎ ተደጋጋሚ መግለጫ ሰጥቷል። የሚያሳዝነውና የሚገርመው ሕወሓት በአማራና በአፋር ክልሎች በወረራ በቆየባቸው አምስት ወራት፤ በ110 ከተሞች ከ3ሺህ በላይ የጤና ተቋማት የወደሙና የተዘረፉ ቢሆንም አንዳቸውም በዚህ ድርጅት የመረጃ ቋት አልተመዘገቡም። ዛሬ ስለዩክሬን የሚንዘረዘረው ዋና ዳይሬክተር ተብዬም ትንፍሽ አላለም። ይህ ድርጅቱም ሆነ ዋና ዳይሬክተሩ ገለልተኛ ላለመሆናቸው ጥሩ አብነት ነው። ይባስ ብሎ የድርጅቱን ሀብትና ያለውን ኃላፊነት ለአሸባሪው ሕወሓት የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ድጋፍ ማሰባሰቢያ አቋራጭ መንገድ እንዳደረገው በገሀድ እየታዘብን ነው።

የሽብር ኃይሉ በዘረፋቸውና ባወደማቸው የጤና ተቋማት የተነሳ የሚሊዮኖች ጤና ለአደጋ ሲጋለጥ፤ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ነፍሰ ጡር እናቶች፣ ህጻናት፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የስኳርና የሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህሙማን መድኃኒት፣ ክትትልና ሕክምና ባለማግኘታቸው ሕይወታቸው ሲያልፍ፤ ለከፋ የጤና ችግር ሲዳረጉና የእናቶችና የህጻናት ክትባት ሲስተጓጎል ትንፍሽ ያላለው ዋና ዳይሬክተር፤ ድርጅቱ ሕወሓት ላመጣው ቀውስ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያን መንግስት ተጠያቂ ሲያደርግና የአገሪቱን ገጽታ ጥላሸት ሲቀባ መንግስት እዚህ ግባ የሚባል ጠንካራ ተቃውሞ እንኳ ማሰማት አልቻለም። በተመሳሳይ ልሒቃን፣ የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ አይደለም። የዩኒቨርሲቲ መምህራንና በቀጥታ የሚመለከታቸው የሙያ ማህበራት ሌላው ቢቀር እንኳ ነጠላ መጣጥፍ በውጭ ጋዜጦችና መጽሔቶች እንኳ ሲጽፉ አናይም።

የአገር መሪዎች፣ ፖለቲከኞችና የአደባባይ ምሁራን በተለይ የምዕራባውያኑ አስተያየታቸውን፣ አቋማቸውን፣ ፖሊሲዎቻቸውንና የግል አመለካከታቸውን እንደ ማንኛውም ተራ ዜጋ እንደ ፋይናንሸያል ታይምስ፣ ዋሽንግተን ፖስት፣ ኒውዮርክ ታይምስ፣ ዎል ስትሬት ጆርናል፣ ደይሊ ቢስት፣ ዘ አትላንቲክ፣ ዘ ጋርዲያን ፣ ታይም፣ ዘ ኢኮኖሚስት፣ ኒውስዊክ፣ ወዘተረፈ ባሉ ዓለም አቀፍ ጋዜጦችና መፅሔቶች በመጻፍ በ(Op - ed) ይገልጻሉ፡፡ Op-ed የopposite editorial ምህጻረ ቃል ሲሆን፤ የጋዜጣው ወይም የመፅሔቱ ተቀጣሪ ባልሆነ ተጋባዥ ወይም በራሳቸው ፍላጎት አስተያየታቸውንና አቋማቸውን የሚያንጸባርቁበት መጣጥፍ ነው ፡፡ ከምህጻረ ቃሉ እንደምንረዳው መጣጥፉ ከጋዜጣው ወይም ከመፅሔቱ ርዕሰ አንቀፅ ጋር ሊቃረን ይችላል፡፡ የጋዜጣው ወይም የመፅሔቱ አቋም ላይሆንም ይችላል፡፡

በአገራችን መሪዎችና ፖለቲከኞች ይቅርና በልሒቃኖቻችን ብዙ ባልተለመደ ሁኔታ ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ በዚያ ሰሞኑን በታዋቂው የቢዝነስና የኢኮኖሚክስ መሰናዘሪያ ‘ የፖሊሲና የፖለቲካ አምድ ላይ በስማቸው ፣ “ What African Economies Need to Survive the Coronavirus? “/ “ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሮና ቫይረስን ለመቋቋም ምን ይፈልጋል? “ / በሚል ርዕስ ለንባብ አብቀተዋል፡፡ ካልዘነጋሁ ከዚህ በፊት ወይም በኋላ “ዋሽንግተን ፖስት” ላይ ይመስለኛል በኦፔድ ጽፈዋል። ሰሞኑን ደግሞ ለ3ኛ ጊዜ በአንባቢዎቹ ዘንድ አንቱታን ባተረፈው” ዘ ኢኮኖሚስት “ መፅሔት ላይ “ Democracy in Africa “ በተሰኘ አምድ ላይ “ Threats to Ethiopia’s democratic transition “ በሚል ርዕስ ማለፊያ መጣጥፍ በግብዣ በመከተብ ሰልሰዋል። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝም “ፎሪን ፖሊሲ” ላይ ጽፈው አንብቤያለሁ። ይህ ብዙ ያልተሄደበት የእሳቸው ፋና ወጊ መንገድና ዳና ይበል የሚያሰኝና ሊከተሉት የሚገባ ነው፡፡ እንደ ትህነጉ ዲጅታል ወያኔ፣ የሸኔ ደጋፊዎችና ግብፅ ያሉ ሀይሎች ሌት ተቀን በተናበበና በተመጋገበ ዘመቻ የሚነዙትን መርዝ ማርከስ የሚቻለው ዓለም አቀፍ ሚዲያውን በአግባቡ መጠቀም ሲቻል ነውና ልሒቃን፣ ፖለቲከኞች፣ ምሁራንና የመንግስት የስራ ኃላፊዎች እንደ ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር የተጣለባቸውን ታሪካዊ ኃላፊነት ሊወጡ ይገባል።

ወደ ቀደሙት መጣጥፎቼ መቋጫ ስመለስ፡ - አሸባሪው ሕወሓት ይህን የሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም የተናጠል የተኩስ አቁም እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የአማራና የአፋር ክልሎች በሕዝባዊ ማዕበል በመውረር፤ በጭና ፣ በንፋስ መውጫ ፣ በጋሊኮማ፣ በአጋመሳና በወረራቸው ሌሎች አካባቢዎች ትህነግ በዘር ማጥፋት፣ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ በሚፈጸም ወንጀል እና በጦር ወንጀለኝነት የሚያስጠይቀውን ጅምላ ጭፍጨፋ ፈጽሟል። ህጻናትን ሴቶችን አረጋውያንን መነኮሳትን በቤተሰባቸው ፊት በጠመንጃ በማስፈራራት በቡድን አስገድዶ ደፍሯል። ሌሎች ለመናገርም ሆነ ለማድመጥ የሚከብዱና እውነት ይህ ወራሪና የሽብር ኃይል ከትግራዋይ፣ ከኢትዮጵያውያን እና ከሰው ልጅ አብራክ የተገኘ ነው የሚል ጥያቄ የሚያስነሱ ነውሮችን ፈጽሟል። በመጀመሪያ በሰሜን ዕዝ በኋላ በማይካድራ የፈጸመውን የክህደትና የጦር ወንጀል እንዲሁም የዘር ማጥፋት ወንጀል በልኩ በተጠናና ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ የተግባቦት የሕዝብ ግንኙነት ስራ ባለመስራታችን ብዙም ያልተጋለጠው ያልተጠየቀውና ያልተከሰሰው ከሀዲው ሕወሓት የልብ ልብ ስለተሰማው በወረራ በያዛቸው አካባቢዎች የማይካድራን ዘር ማጥፋት የሚያስንቅ የዘር ማጥፋት ሊፈጽም ችሏል።

ወደ 10ሺህ፤ የሚጠጉ የጤናና የትምህርት ተቋማት ተዘርፈዋል። ወድመዋል። የወሎ፣ የወልድያና የመቅደላ ዩኒቨርሲቲዎች እና የሰቆጣ የመምህራን ኮሌጅ ተዘርፈዋል። ወድመዋል። የሕዝቡ ሀብት ንብረት ተዘርፏል። በተረፈው እንዳይገለገል ሆን ተብሎ እንዲወድምበት ተደርጓል። አብያተ ክርስቲያናት እና መስጊዶች ረክሰዋል። ወታደራዊ ካምፕ፣ ምሽግና የከባድ ጦር መሳሪያ ማጥመጃ ሆነዋል። በከባድ መሳሪያ ተደብድበዋል። መጽሐፍ ቅዱሳት፣ ቅዱስ ቁራኣናትና ሌሎች መንፈሳዊ መጽሐፍት ሆን ተብሎ ተቃጥለዋል። የተረፉት እየተቀዳደዱ መጸዳጃ ሆነዋል። በአፋርና በአማራ ክልሎች በተለይ በኮምቦልቻና አካባቢው ከ40 በላይ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ተዘርፈዋል። ወድመዋል። በዚህ የተነሳ በ10ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰራተኞች ስራ አጥተዋል። ከተሞች መርፌ ሳይቀር ተዘርፈዋል። እርቃናቸውን ቀርተዋል። ለዚህ ነው ነዋሪዎች ኮምቦልቻ፣ ደሴ፣ ወልድያና ሌሎች በወራሪው ስር የነበሩ ከተሞች ወደ መቐሌ ተጭነው ሔደዋል የሚሉት። የቀሩት እርቃናቸውን ነው ለማለት።

በሁለቱ ክልሎች የተዘረፈውና የወደመው ሀብት ወደ ግማሽ ትሪሊዮን ብር ይገመታል። ከተሞች 20 እና 30 አመታት ወደኋላ ተመልሰዋል። ለዘመናት በላቡና በደሙ ያፈራው የአርብቶና የአርሶ አደሩ ጥሪት ተዘርፏል። እንደ ልጆቹ የሚያያቸው እንስሳት ታርደው ተበልተዋል። የተረፉት በጥይት ተደብድበው ተገለዋል። የሚያሳዝነው ዛሬም ይህን ኅልቆ መሳፍርት የሌለው ወንጀል ሰው ሰው የሚሸቱ ወቅታዊ መልዕክቶችን ቀርጸን፤ እንደ ታዳሚው ስብጥር የተቃኙ መረጃዎችን በፈጠራ አዋዝተን ማቅረብ አልቻልንም። በዚህ የተነሳም እውነትንና ፍትሕን ይዘን በሀሰተኛ መረጃ ብልጫ ተወስዶብናል። የአስገድዶ መድፈር ተጠቂዋ የሽዋሮቢቷ ኢክራም ለብቻዋ በራሷ ተነሳሽነት ወደ ሚዲያው በመምጣት የፈጠረችውን ተጽዕኖ ያህል እንኳ መፍጠር አልቻልንም ። ሰሞነኛውን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ አስደንጋጭ ግኝት ዓለም አቀፍ አጀንዳ በማድረግ የሕወሓትን ምንደኞችና አለቅላቂዎች አንገት ማስደፋት ስንችል በመናኛ ዜና ብቻ አልፈነዋል። ሆኖም ዛሬም አልረፈደምና ስህተታችን ሊታረም ይገባል።

እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ኢክራምንና ዘሐራን ጨምሮ በየከተሞች የአስገድዶ መድፈር ፤ የግድያ፣ የሰብዓዊ መብት ጥቃትና ስቃይ ሰለባ የሆኑ ዜጎችን ሕመም እንዲያመን እንዲሰማን በማድረግ የማይናቅ ጥረት አድርጓል። በዚያ ሰሞን “ስለኢትዮጵያ” በሚል ርዕስ ያሰናዳው የፎቶግራፍ አውደ ርእይ ይህን የታሪክ ጠባሳ ሰዋዊ አድርጎ ለሕዝብ አቅርቧል። አሁንም ቢዘገይም አልረፈደምና ሚዲያዎቻችን፤ የመንግስት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና ፕሬስ ሴክሬታሪያት ሪፖርት ማንበብን ቀነስ አድርገው ፤ የደለበውንና በእጃቸው ያለውን የተግባቦት ግብዓት በጥበብ ሊጠቀሙበት ይገባል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ህጻናትና ሴቶች በቡድን ተደፍረው ፤ በሺህዎች የሚቆጠሩ በግፍ ተገድለው ፤ የጅምላ መቃብራቸውን ታቅፈን ፤ ወደ 10ሺህ የሚጠጉ የጤናና የትምህርት ተቋማት ወድመው ፤ በሰሜን ዕዝ ላይ በተፈጸመ ጥቃት ወደ ጦርነት ተገደን ገብተን፤ ወዘተረፈ እንዴት የሕወሓትን ሽብር፣ የጦር ወንጀል፣ የዘር ማጥፋት፣ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል፤ ወዘተረፈ ለዓለም ማጋለጥ ያቅተናል !?

የተግባቦት (ኮሙኒኬሽን)ስራዎቻችን ሶስት ዋና ዋና ልምሻዎች አሉባቸው። የመጀመሪያው በጥበብና በፈጠራ ስራዎች በማዋዛት መረጃዎች ሰው ሰው እንዲሸቱ የማድረግ ፤ ሁለተኛው ተደራሲዎችን(ኦዲየንስ) የመለየት ሲሆን፤ ሶስተኛው ደግሞ መልዕክቱን በአግባቡ የመቅረጽ ችግሮች ናቸው። በተለይ የቀውስና የጦርነት ጊዜ የተግባቦት ስራዎች ለሰው ልጅ ስሜት የቀረቡ ሆነው መቀረጽ አለባቸው። ወሰን ፣ ዘር ፣ ቀለም ፣ ጾታ ፣ እድሜ ፣ ሀይማኖት ፣ ርዕዮተ ዓለም ፣ መደብና ሌላ ልዩነት ሳይገድባቸው መላ የሰውን ልጅ ስሜት ገዝተው ለድርጊት የሚያነሳሱ መሆን አለባቸው። ከዚህ አንጻር ያለፉት ሶስት አመታትን በተለይ ደግሞ ያለፈውን አመት መለስ ብለን ስንገመግመው አፍን ሞልቶ ድከመቱን መናገር ይቻላል።

ከሀዲውና እፉኝቱ ትህነግ/ሕወሓት ባለፈው አንድ ዓመት በሕዝቤ በአገሬና በሰሜን ዕዝ ከፈጸመው ኅልቆ መሳፍርት ከሌለው ለመስማት የሚሰቀጥጥ ለማየት ከሚዘገንን ሰቆቃ ፣ ግፍ ፣ ጭፍጨፋ ፣ ዘረፋ ፣ ውድመት ፣ ወዘተረፈ ባልተናነሰ ዛሬ ድረስ እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበኝ አገሬ ሕዝቤ ሰራዊቴና መንግስቴ የክህደትና የጥቃት ሰለባ ሆነው እያለ ተወጋዥ፣ ተከሳሽና ተወቃሽ መሆናቸው ነው። እውነትንና ፍትሕን ታቅፈው ባዶ እጃቸውን አጨብጭበው መቅረታቸውን ሳስብ ጥርሴን እያፋጨሁ እቃትታለሁ። እቃጠላለሁ። እበግናለሁ። እናም እላለሁ፤ “ብዙኃን መገናኛዎቻችንና አምባሳደሮቻችን ከመከላከል እሳት ከማጥፋት አባዜ አሁኑኑ ይውጡ !”፡፡

ማህበራዊ

የሕይወት ገጽታ

በስኬት የታጀበችው፤ ሩጫዋን ያልገታችው ወጣት

ሰላማዊት ውቤ

-ጋዜጠኛና ደራሲ ፍሬዘር ዘውዴ

በምድራችን የትኛውም ያስ እንቅፋት አልጋ በአልጋ በሆነ መንገድ የተጓዘ ሰው የለም። በተለይ የሴት ልጆች ጉዞ እንደ ዕድል ሆኖ እንቅፋት አያጣውም። ሥራ ፈልገው የሄዱትን ለአብነት ብንጠቅስ ዝቅ ተደርጎ መታየት ይገጥማቸዋል። የተለየ ፍላጎት የሚያሳድርባቸውና አላስፈላጊ ጥያቄ የሚያቀርብላቸውም አለ። ሴቶችን ወደ ኋላ የሚያስቀሯቸው ነገሮች ብዙ ናቸው። በሕይወት ዘመናቸው ማግኘት ሲገባቸው የሚያጡትም ያይላል። ይሄኔም ጥሉ ያልጣላቸው ልባሞች ሴቶች መባነናቸው አይቀርም። እንቅፋቶች አእምሯችንን ባይሰርቁን ኖሮ ምን አልባት የበለጠ ደረጃ ላይ እንገኝ ነበር ይላሉ። "ድሮ ገናም የምንፈልገውን መሆን እንችል አልነበረም እንዴ?" ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። አለመርፈዱን ተስፋ አድርገውም ካሰቡበት ለመድረስ ስሌሉት አጋሮቻቸው አርአያ የሚሆን ሩጫቸውን ይቀጥላሉ።

ከነዚህ ልባም ሴቶች መካከል አንዷ የሆነችው የዛሬ የሕይወት ገጽታ እንግዳችን ወይዘሪት ፍሬዘር ዘውዴ በብዙ የሕይወት ውጣ ውረዶች ተፈትናለች። የፈተናው ጫና 30 ሳይሆን 70 እና 80 ዓመት የኖረች እስኪ መስላት ቀምበሩ ከብዶባታል። በመቻሏ ተጠራጥራ በሕይወት ዘመኗ ተስፋ እንድትቆርጥና እንድታዝን አድርጋታል። ቢሆንም ሳትሸነፍለት ዛሬም ያሰበችበት ለመድረስ የሚያስችሳትን ጥረት በማድረግ ላይ ነች። የኪነ ጥበብ እና ጋዜጠኝነት ዝንባሌዋን በእጇ ለማድረግ የሄደችበት ርቀት ያስደምማል። ሁለቱን ጥምር ሙያዎች ያቀፈ ዓለም አቀፍ ካምፓኒ ለማቋቋም ያሰበችው ሬዕይዋ ይበረታታል። ያለፍላጎቷ የተማረችውን ትምህርት ከጫንቃዋ በማውረድ በምትወደው መስክ ለመሥራት የተከተለችው ስልትም ያስተምራልና እንሆ ተሞክሮዋን ተካፈሉልን።

ምጥን ጭብጥ

ፍሬዘር ዘውዴ ትባላለች። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት ኤጀንሲ በከፍተኛ የኮሚኒኬሽን ባለሙያነት እየሰራች ትገኛለች። የኪነጥበብና የጋዜጠኝነት ጥምር ተስጥኦ ያደረባት ገና ብላቴና ሳለች ነው። ተማሪ በነበረችበት ወቅት ክፍል ውስጥ እሷ ግጥም ሳታነብ የአማርኛ ትምህርት እንዳይጀመር በማድረግ መምህሯ እያበረታቷት ነው ችሎታዋን እያጎለበተችው የመጣችው። በትርፍ ሰዓቷ በነዚሁ ላይ እየሰራች ትገኛለች። መረዋው ድምጿ በምትሰራባቸው የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በአድማጮቿ ዘንድ ተወዳጅነትን አትርፎላታል። ተቋማቱንም ታዋቂ አድርጓቸዋል። ከእነዚህ መካከል ሰለሞን ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ከኢቢሲ ጋር በመተባበር በሚያቀርበው አዲስ አውቶሞቲቭ ፕሮግራም በከፍተኛ አዘጋጅና አቅራቢነት የምትሰራበት፣ በኤዲተር ኢን ቺፍ የምትሰራበት ሀበሻ ኤክስፖት ዩቲዩብ ቻናል ይጠቀሳሉ። ፍሬዘር venufrez የተሰኘ የራሷ ዩቲዩብ ቻናልም ያላት።

ፍሬዘር በተደጋጋሚ የጉብኝትና የትምህርት ግብዣ ሲያቀርብላት ከኖረው ከኢራን ኢምባሲ ጋር በሴቶች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ታቀርባለች። በስልጠናም ትሳተፋለች። "የፍቅር ገፆች" (ሚያዝያ 2007) በሚል ርዕስ የራሷ መጽሐፍም አሳትማለች። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በሰራችበት ወቅት ዩኒቨርሲቲው አሰባስቦ "ይድረስ ለሟቹ እና ሌሎችም..." በሚል ርእስ ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥም ሥራዎቿ ተካትተዋል። አሁን ላይ በጋዜጠኝነትና በኪነ ጥበብ ዘርፉ ትልቅ ካምፓኒ የመክፈት ራዕይ ሰንቃ በመንቀሳቀስ ላይ ነች። እንቅፋቱ በዝቶ ባያደነቃቅፋት ራዕዩ ዕውን መሆን ያለበት ድሮ እንደነበር ብታምንም አሁንም አለመርፈዱ ላይ ከራሷ ጋር ትስማማለች።

ልጅነትና ዝንባሌ

የተወለደችው በ1982 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ልዩ ስሙ ቀራንዮ መድኃኒዓለም በተሰኘ አካባቢ ነው። ያደገችውም እዚሁ ሲሆን አስተዳደጓ ጠበቅ ያለና ከሌሎች ልጆች ለየት የሚል ይመስላል። ምክንያቱም በሙያቸው ሲቪል ኢንጅነር የሆኑት ወላጅ አባቷ ዘውዴ ሁንዴ፤ እንዲሁም በሙያቸው የሂሳብ ባለሙያ (አካውንታንት) የሆኑት ወላጅ እናቷ ወይዘሮ ቀፀላ በለጠ የዋዛ አልነበሩም። ትልቅ ትኩረት ይሰጡ የነበረው ለትምህርት ነው። ልጆቻቸው በሙሉ ትኩረታቸው ትምህርትና ትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲሆን ከመፈለጋቸው የተነሳ ጊዚያቸውን በበዛ ጨዋታ እንዲያሳልፉ እንኳን አይሹም ነበር። በተለይ ነፍስ እያወቁና ዕድሜያቸው ወደ ታዳጊነት እየተሸጋገረ ሲመጣ ከቤት መውጣትም የተከለከሉበት ጊዜ አለ።

ከኢንጅነር ዘውዴና የሂሳብ ባለሙያዋ ወይዘሮ ቀፀላ ከተወለዱት ልጆች መካከል ፍሬዘር በተለይ የኪነ ጥበብ እና የጋዜጠኝነት ዝንባሌ ያላት መሆኗ በወቅቱ በወላጆቿ ፈፅሞ አልተወደደላትም ነበር። በጥናት ወቅት የተዘረጋ ደብተሯን ከለላ አድርጋ ረጃጅም እና አጫጭር ልቦለድ ታነባለች። ግጥሞችን ትጽፋለች። መገናኛ ብዙሃን ትከታተልና በዚሁ ላይም ንቁ ተሳትፎ ታደርጋለች። ሆኖም ወላጆቿ ይሄ ዓይነቱ ዝንባሌዋ በተለይም የተለያዩ መጽሐፍቶችን ከየትም ከየትም ብላ ተውሳ ወደ ቤት አምጥታ ማንበቧ በፍፁም አልተመቻቸውም። "የትምህርት ጊዜዋን ይሻማና ያሰንፋታል" በሚል ስጋት በጥናት ክፍሏ ውስጥ ከትምህርቷ ውጭ ምንም ነገር እንዳትሰራ ክትትል ሲያደርጉባት ነው ያደገችው። ብዙ ጊዜም ተቀጥታ ታውቃለች። የማንበብ ሱሷ ክፍል ውስጥ በአስተማሪም አስይዞና አስገርፏታል። በተለይ መጽሐፍ ስታነብና ጽሑፍ ስትጽፍ ከፍተኛ ተመስጦ ውስጥ ስለምትገባ ወላጅ እናቷ ከኋላዋ መጥተው ሲቆሙ እንኳን አታያቸውም። የምታነብበውን መጽሐፍ የሚወስዱባት ነገር ያበሳጫት እንደነበርም ታስታውሳለች።

ትምህርት

ትምህርትን አሀዱ ብላ የጀመረችው ‹ህሊና› በተባለ አፀደ ህፃናት ነው። እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለውን ትምህርቷን "ቀራንዮ መድኃኒዓለም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት" ሲሆን፤ የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ትምህርቷን ደግሞ ጦር ኃይሎች አካባቢ በሚገኝ ‹ፋሚሊ› የተሰኘ የግል ትምህርት ቤት ነው የተከታተለችው። የዘጠነኛ እና የ10ኛ ክፍል ትምህርቷንም ኮልፌ ኮምፕሪንሲቭ በመማር አጠናቃለች። የ10ኛ ክፍል ፈተናን (ማትሪክ) ጥሩ ነጥብ በማምጣት አልፋ አዲስ ከተማ መሰናዶ ትምህርት ቤት ገብታ ተምራለች።

ለማህበራዊ ሳይንስ ልዩ ፍቅር ሲኖራት የታሪክ ትምህርትን አብዝታ ትወደው ነበር። የማህበራዊ ሳይንስ መስኩን ከመውደዷና ከጉጉት የተነሳ ገና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ሳለች "መቼ ነው መሰናዶ ገብቼ የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪ ነኝ የምለው?" የሚል ሀሳብ በልቦናዋ እስከማጠንጠን ደርሳለች። ማትሪክ ተፈትና ስታልፍ "ኤ" ካመጣችበት የኢንግሊዝኛ ትምህርት በተጨማሪ ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገበችባቸው የትምህርት ዓይነቶችም ዋናዎቹ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች ነበሩ።

ፍሬዘር የመሰናዶ ትምህርቷን በከፍተኛ ነጥብ አጠናቅቃ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት በቅታለች። ሆኖም በወቅቱ ምርጫን መሰረት ያደረገ ምደባ ለማካሄድ ይቻል ዘንድ ይሞላ የነበረውን ፎርም ባለመሙላቷ ባለው ቦታ እንድትመደብ ግድ አለ። በመሆኑም ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ተመደበች። ወላጅ እናቷ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሕግ እንድታጠና ይፈልጉ ነበር። አባቷ እንዲያሳምኗት ለማድረግም ሞክረዋል። አባቷም ቢሆኑ የእናቷን ያህል ተጭነው ባይሆንም ሀሳቡን እንደ ሀሳብ ሳያቀርቡላት አላለፉም። እሷ ግን ልቧ ውስጥ ያለው ጥበብ ነው።

እንኳን ትምህርት ለማማረጥ ከትምህርት ቤት ቤት፤ ከቤት ትምህርት ቤት እንጂ ከቤት ወጥታና ውጭ በማደር ከወላጆቿ ተለይታ ለማታውቀው የያኔዋ ታዳጊ ፍሬዘር ጎንደር መመደብ ከባድ ነበር። ከቤተሰብ መራቁና ናፍቆቱ ቀርቶ አካባቢውንና ሁኔታዎችን መልመዱ በራሱ ያሳደረባት ጫና ቀላል አልነበረም። ከቤተሰብ መለያየቱ እጅግ አስከፍቷታል። እሷ ባለችበት ዕድሜ ከቤተሰብ ተለይቶና ለብቻ ቤት ተከራይቶ መኖር እንደሚቻል እንኳን ከዩኒቨርሲቲ ከወጣች በኋላ ነው ያወቀችው። ይሄም ቢሆን በወቅቱ ለእሷ ፈፅሞ በአእምሮዋ የሚታሰብ አልነበረም። በአጠቃላይ በፍፁም ደስተኛ አልነበረችም። ጫናውንም በቀላሉ መቋቋም ተሳናት።

ያም ሆነ ይህ ፍሬዘር በምስራቅ አፍሪካና በልማት ጉዳይ ላይ የሚያወራውንና "ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኢንቫይሮመንታል ማኔጅመንት ስተዲ" የተሰኘውን ትምህርት ክፍልን መቀላቀል የመጀመሪያ ምርጫዋ አደረገች። በሲሳይ ንጉሱ «ሰመመን» መጽሐፍ የምታውቀውን የዩኒቨርሲቲ ሕይወት ከራስዋ ጋር ለማጣጣም መፍጨረጨሯን ቀጠለች።

ሆኖም ፍሬዘርን ከትምህርት ክፍሉ ከዚህ ቀደም ብሎ ለዩኒቨርሲቲ በነበራት አመለካከት የምትጠብቀውን አላገኘችበትም። ፈተና ከየትኛው ክፍል ነው የሚወጣው ተብሎ የሚጠየቅበት፣ በተለያየ ብልጠት ነጥብ ለማምጣት የሚኬድበት ሂደት እሷ እንደምትፈልገው አልነበረምና ምቾት አልሰጣትም።

እንደውም በወቅቱ 18 ዓመት የሞላት ወጣት ከመሆኗ፤ እየበሰሉች ከመምጣቷና ተጨማሪ ሀላፊነቶች ከመምጣታቸው ጋር ተዳምሮ "ፍላጎቴ ይህ አልነበረም" የሚል ሀሳብ በአእምሮዋ ይመላለስ ጀመር። ወደዚሁም በትምህርት አሰጣጡ እጅግ ጥብቅ ከሆነው ጎንደር ዩኒቨርሲቲ "በትምህርቴ ደካማ ሆኜ እባረር ይሆን?" በሚል ስጋትም ነበር። ያ ሁሉ ሆኖ ግን በመጀመሪያው ዓመት ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ቻለች።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሥነጽሑፍ ዝንባሌ

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ የሥነ ጽሑፍ ዝንባሌዋ አሸነፋት። የዩኒቨርሲቲውን ባህል ማዕከል እንድት ቀላቀልም አስገደዳት። በማዕከሉ ግጥሞቿን ማቅረብና የተለያዩ መርሐ ግብሮች ላይ መሳተፍ ጀመረች። የተለያዩ የግጥምና ሥነ ጽሑፍ ውድድሮችን የማሸነፍ ዕድልም አገኘች። ጎንደር የሚገኘው የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር አባል ሆነች። በማህበሩ አባል መሆኗ አዳዲስ መጽሐፎችን ተውሶ ለማንበብ ሰፊ ዕድል ከመፍጠር ባሻገር የሥነ ጽሑፍ ጥማቷን የምትወጣበትን መድረክ አልጋ በአልጋ በማድረግ አግዟታል። ሆኖም የሥነ ጽሑፍ ዝንባሌዋ አሁንም በዩኒቨርሲቲው ለጀመረችው ትምህርት ፈተና እንደሆነባት ላስተዋሉት መምህራኖቿ አልተዋጠላቸውም። መምህራኖቿ በተመደቡበት ትምህርት ክፍል ደስተኛ እንዳልሆነች ያውቁ ነበርና ዝም ብለው አላስተዋሏትም። በትምህርት ክፍሉ ደስተኛ ባትሆንም ትምህርቷን በውጤታማነት መማርና ማጠናቀቅ የሚያስችል ጥሩ አቅም እንዳላት በተደጋጋሚ ነገሯት። የትምህርትና ጥናት ጊዜዋን በሥነ ጽሑፍ ባህል ማዕከል በተለያዩ መርሐ ግብሮች በመሳተፍ እንዲሁም መጻሕፍትን በማንበብ ታሳልፍ ነበር። ይህም ውጤቷ እንዲቀንስ እያደረጋት መጣ። ውጤቷ በመቀነሱም መምህራኖቿ ደስተኛ ሊሆኑ አልቻሉምና በግልፅ ይገስጿት ነበር። በተለይ ያኔ ዶክተር የነበሩትና ዛሬም በዛው በጎንደር ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እያገለገሉ የሚገኙት ፕሮፌሰር ሲሳይ ምስጋናው ለሥነ ጽሑፉም ሆነ ለጋዜጠኝነት ሙያ የነበራት ዝንባሌ የትም እንደማይሄድና ውስጧ ያለ በመሆኑ "ወደፊት ትደርሽበታለሽ አሁን ላይ ትኩረትሽን ትምህርትሽ ላይ አድርጊ" ሲሉ ብዙ ጊዜ መክረዋታል። የመጀመሪያ ዲግሪዋን በ"ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኢንቫይሮመንታል ማኔጅመንት ስተዲ" ጥናት መስክ አጠናቅቃ ከወጣች በኋላም ሁለተኛ ዲግሪዋንም ሆነ የሥራ መስክዋን በምትወደው የጋዜጠኝነት ሙያ ዘርፍ እንድታደርግ ያበረታቷት እኚሁ ፕሮፌሰር በመሆናቸው ባለውለታዋ ናቸው።

የወጣቷ ባለውለታዎች ተቆጥረው አያልቁም። ብቃቷን ያስተዋሉና ጥሩ አቅም እንዳላት ያረጋገጡ ሁሉ ዛሬ ላለችበትና ለደረሰችበት ደረጃ የየራሳቸውን አስተዋጾ በማድረግ ታግለውላታል። ከነዚህ አንዱ በወቅቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ረዳት ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ ናቸው።

ፕሮፌሰር ሲሳይ ምስጋናው ወደምትወደውና ከሥነ ጽሁፍ ተስጥኦዋ ጋር ወደ የሚቀራረበው የጋዜጠኝነት ሙያ እንድትገባ ቢያበረታቷትም ፍላጎቷን ዕውን

ማህበራዊ

የሕይወት ገጽታ

በማድረግ መሬት በማስነካቱ ረገድ የፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ አስተዋጾ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብታ የሁለተኛ ዲግሪዋን ለመማር የሚያስችላትን የመግቢያ ፈተና ካለፈች በኋላ በሙያው ያላትን የካበተ አቅምና ልምድ በማየት ሥራዋን እየሰራች ትምህርቷን በቀኑ ክፍለ ጊዜ እንድትከታተል ፕሮፌሰር ነብዩ ባዬ ፈቅደውላታል።

ያም ሆነ ይህ ፍሬዘር ጎንደር ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራም ተማሪ በነበረችበት ወቅት የነበረው የወጣቷ የሥነ ጽሑፍ እና የጋዜጠኝነት ሙያ ዝንባሌ በዩኒቨርሲቲው "ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኢንቫይሮመንታል ማኔጅመንት ስተዲ" መስክ ትከታተል ለነበረው ትምህርቷ እንቅፋት ከመሆን አልተመለሰም።

ሙሉ ትኩረቷ ቅን ለሁለቱ ዝንባሌዎቿ በመስጠቷ ዋናውንና የመጀመሪያ ዲግሪ ሥራዋን ረስታዋለች። የረሳችበት ሁኔታ ደግሞ አስገራሚም አስቂኝም ነው። በአንድ የፈተና ዕለት እንደሌሎች ተማሪዎች ፈተናው እስኪጀመር ፈተና ክፍል ውስጥ ተቀምጣ ነበር። ሰርክ በየደረሰችበት ሥፍራ በአእምሮዋ የመጣላትን ሀሳብ የምታሰፍርበት ብዕርና ወረቀት ከእጅዋ የማይጠፋው ፍሬዘር ፈተናው እስኪጀመር በሚል ብዕርና ወረቀቷን አውጥታ ግጥሟን መፃፍ ትጀምራለች። በዚሁ ትመሰጥናም ጭራሽ ፈተናውን ትረሳዋለች። ሌሎቹ ተማሪዎች በፊናቸው ለፈተናው ከተሰጠው ሰዓት ገሚሱን አገባደዋል። ፈተናውን ሰርተው ጨርሰው የወጡ ተማሪዎችም ነበሩ።

በዚህ አይነቶቹ ሁኔታዎች ፍሬዘር ብዙ ጊዜ ከመምህራኖቿ ጋር ሁሉ ትጋጭ ነበር። ታዲያ ከዚህ ድርጊቷ እንድትታቀብ በወቅቱ ፕሮፌሰር ሲሳይ ምስጋናውን ጨምሮ በትምህርቷ ትልቅ ብቃት እንዳላት የሚያውቁ መምህራኖቿ ትምህርቷን ትኩረት ሰጥታ እንድትከታተል ሳያሰልሱ መክረዋታል።

መድረክ የመምራት ልምድ

ፍሬዘር መድረክ የመምራት ልምድ የቀሰመችው በዚሁ በካምፓስ ቆይታዋ ነው። የስርዓተ ጾታ እና የኤች አይ ቪ/ኤድስ ክበባት አባል መሆኗ ለመምራቱ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላታል። በዚህ ውስጥ የሕይወት ስልጠና ማግኘት ችላለች። "የሕይወት ክሂሎት ስልጠና" አሰልጣኝም ለመሆን አብቅቷታል። ዩኒቨርሲቲው እሷን ጨምሮ ሌሎች ተማሪዎቹን ባስመረቀበት በዛው ዓመት ኪነ ጥበብና ባሕል ማዕከል ላይ የነበሩ ወጣቶች በየምሽቱ ያቀረቧቸውን ሥራዎች በማሰባሰብና ከዚያ ላይ በመምረጥ "ይድረስ ለሟቹ እና ለሌሎቹም" በሚል ርዕስ መጽሐፍ አሳትሞ ነበር። ታዲያ በዚሁ በ2003 ዓ.ም በታተመ መጽሐፍ ላይ የእሷም የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ተካትተው ወጥተውላታል። ወጣቷ የተዋጣላት ጸሐፊና ንግግር አዋቂ ከመሆንዋ አንፃር ለጋዜጠኝነት ሙያ መስክ የምታደላ ነች። በመመረቂያዋ ዓመት መጨረሻም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ወጣቶች ፕሮግራም ላይ ቀርባ መድረክ የመምራትና የንግግር ችሎታዋን አስመሰከረች። ቀደም ሲል በሬዲዮ ጣቢያዎች የነበራትን ተሳትፎ አጠናከረች። በደምሳሳው ይሄ የዩኒቨርሲቲ ቆይታ የተለያዩ ሥራዎችን በውጤታማነትና በፍጥነት መሥራት የቻለችበት ወቅት ነበር። ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀችውም ከብዙ ዓላማና ተስፋ ጋር ነው። ከካምፓስ ስትወጣም ትልቅ ህልም ነበራት። የትኛውንም ዓይነት ሥራ መሠራትና ብዙ ነገር ማድረግ እችላለሁ ብላም አስባለች።

ከዩኒቨርሲቲ በኋላ

እንዳሰበችው ህልሟን የምታሳካበት መንገድ አልጋ በአልጋ አልሆነላትም። ዋናው ምክንያት ደግሞ በተመረቀችበት ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኢንቫይሮመንታል ማኔጅመንት ስተዲ የተሰኘው የትምህርት መስክ አገሪቱ ውስጥ በተለይም ደግሞ እሷ ተወልዳ አድጋ ትኖርበት በነበረው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሥራ አለመኖሩ ነው። እሷ ተመረቃ ወደ አዲስ አበባ በተመለሰችበት ወቅት በትምህርቱ መስክ ቀድመው የተመረቁም ሥራ አለማግኘታቸው በእጅጉ አሳሰባት። ሥራ ፍለጋ ሲንከራተቱ ማየቷ ምነው ትምህርቱን ባልተማርኩ በሚልም አስቆጫት። ጊቢ በነበረችበት ሰዓት ትምህርቱን አቋርጠው የሄዱ ተማሪዎችም ታወሷት። የትምህርቱ ዓይነት አዲስ በመሆኑ ይሁን በሌላ ባይገባትም ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ወጥቶ ለውድድር በምትሄድበት ጊዜ ራሱ በምዝገባ አከናዋኙ ተቋም ሠራተኞች የትምህርት መስኩ ፍፁም አለመታወቁ እንኳን በእጅጉ ገረማት። "ምንድነው ይሄ ሶሻል ሳይንስ ነው ዴቨሎፕመንት?" የሚል ግራ አጋቢ ጥያቄያቸውንም መመለስ ታከታት። ያኔ ስትመደብበት የፈራችው አልቀረላትምና በጣም አሳዘናት። ከሁኔታው የተማረችው ትምህርት የሚያዋጣት አለመሆኑንም በሚገባ ተረዳች። በመሆኑም ፍሬዘር ከዩኒቨርሲቲ ተመርቃ ከወጣች በኋላ ያለውን ጊዜ እንዳሰበችው ቀላልና ተስፋማ ሳይሆን እሾህና ጋሬጣዎች የበዙበት ፈታኝ ሆኖ ነው ያገኘችው።

የሥራ ዓለም

ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀጠረችው በመምህርነት ሙያ ነው። ሥራ የጀመረችውም በግል ትምህርት ቤት ነበር። በሦስት የግል ትምህርት ቤቶች የሰራች ሲሆን ከግል ትምህርት ቤት መምህርነት በኋላ በዲግሪ በተመረቀችበት ስራ ያገኘችው የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት (ወመዘከር)፣ በ2007 ነሐሴ 1 በስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያነት ነበር። ከ2010 መስከረም ጀምሮ በዝውውር ብሔራዊ ቴአትር በስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያነት መጣች። ታኅሳስ 1/2013 በተመረቀችበት ዘርፍ ለመስራት ከብሔራዊ ቴአትር ወደ ወመዘከር በዝውውር መጥታ በከፍተኛ የኮሚኒኬሽን ባለሙያነት እያገለገለች ትገኛለች።

ፍሬዘር ሥራ ለማግኘት ወዳደረገችው ጥረት እንግባና ሥራ ፍለጋ ብሎ መንከራተቱ ሲደክማትና አማራጭ ስታጣ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ የወሰደችው የሕይወት ክሂሎት የአሰልጣኞች ስልጠና ትዝ አላት። በትዝታዋ ውስጥም ምንም እንኳን የፔዳጎጂ ትምህርት ባትወስድም የማስተማር ልዩ ተስጥኦ እንዳላት የተገነዘበችበት ጊዜ መኖሩ ተገለፀላት። ከዚሁ በመነሳትም በዚሁ በጨበጠችው የሕይወት ክሂሎት በመምህርነት ተቀጥራ ለማስተማር የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተወዳደረች። በውድድሩም በጥሩ ውጤት አለፈች። እናም አማርኛና ሲቪክስ ትምህርቶችን ለሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች መስጠት ጀመረች።

ሆኖም ያኔ እሷ በዕድሜ ልጅ ነበረች። በአንፃሩ ተማሪዎቿ ትልልቆች ነበሩ። በዕድሜ ብቻ ሳይሆን በአካልም የጎለበቱ መሆናቸው ለሚያየን ያስቃል። እንደውም አንዳንዴ ወላጆች በሚመጡበት ሰዓት ልጅ ከመሆንዋ የተነሳ ተማሪ እየመሰለቻቸው አስተማሪው የታለ ይሏት ሁሉ ነበር። ሆኖም ፍሬዘር ከዚህ የመምህርነት ሥራዋ ብዙ ነገር አይታና ተምራበታለች።

በተለይ ወላጆች በልጆች ላይ ትልቅ ሚና እንዳላቸው የተማረችበት ሕይወት ነበር። ምክንያቱም ክፍል ውስጥ በምታስተምርበት ጊዜ በተማሪዎችዋ ላይ በጣም አስቸጋሪ ባሕርይ ታይ ነበር። በዚህ በማስተማር ሥራ ሦስት የግል ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎችን ፀባይ የማየት ዕድል አጋጥሟታል። በተለይ ቀረብ አድርጋ ለማናገር በምትሞክርበት ሰዓት ከተማሪዎችዋ የሚያሳዝን ታሪክ ትሰማ ነበር። የብዙዎቹ ወላጆች እንደሌሉ ከኢትዮጵያ ውጭ ዕቃ ሊያመጡ እንደሄዱ ሳይቀር ይነግሯት ነበር። በተለይ ቤት ውስጥ ያለ ችግር ወላጆቻቸው ሳይቀር እየመጡ በትዳራቸው ውስጥ ያለውን አለመስማማት ጭምር ያወሩላት ነበር። "ስታድጉ ምን መሆን ነው የምትፈልጉት?" ስትላቸው አንዳንዶቹ መማር እንደማይወዱና ሲያድጉ ትምህርት የማቆም አላማ እንዳላቸው ይገልፁላታል። እንዲህ ብላ መልስ የሰጠቻት ተማሪ ነገ ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ልትወድቅ እንደምትችል ማሰቡ በራሱ ራስ ምታት ሆነባት ነው የቆየችው።

በዚህም የመማር ዓላማውና ፍላጎቱ ያልነበራቸው ልጆች መኖራቸውን ታዝባለች። በዚህ የተነሳ የማስተማር ሥራውን የጀመረችበት ጊዜ በጣም ብስጩና ቁጡ የሆነችበት ሁኔታ ተፈጥሮባት ነበር። በተለይ ደግሞ እሷ በምን ዓይነት መልኩ እንዳደገች ስታስበው እርስ በእርስ የሚያወሩት ጆሮ የሚጎረብጥ ወሬ በእጅጉ ያስደነግጣትና ይገርማት ሁሉ ነበር። በሶስቱም የግል ትምህርት ቤቶች ያለው ነገር በሙሉ የሚረብሽ ሆነባት። በስተመጨረሻ በዚህ ሁሉ በመጨነቋ ጨጓራና ማይግሬን ያዛት። የፀና የራስ ህመም ውስጥ ገብታ አረፈች። እምትሆነውና የምታደርገው እስኪሳናት ጭንቀቶች ሲደራረቡባት ከመምህርነቱ ሙያ መውጫ መንገድ ሁሉ አልታይሽ እስከማለት ድረስ ደረሰች። ሕይወቷን እስከ መጥላት እንዲሁም ራስዋ ላይ ጥቃት እስከማድረስና መኖር የሉብኝም እስከ ማለት ድረስ ዘለቀች። "ለዚህ ነው እንዴ የጓጓሁት" በማለትም ተፀፀተች። በመምህርነት የሰራችባቸውን ዓመታት በዚህ መልኩ አሳለፈች።

ሴሳኛው የፍሬዘር የሥራ አማራጭ

በሰዎች ጥቆማ አማካኝነት የሜዳ ቴኒስ አሰልጣኝ በነበረውና ሰለሞን ደነቀ፣ የድርጅቱ ስም "ድሪም ቢግ ስፖርት አካዳሚ" በሕዝብ ግንኙነትነት የሥራ ዕድል በማግኘቷ ከመምህርነት ሙያው ተላቀቀች። "የፍቅር ገጾች" (2007 ኢ.ም) የሚለውን ግጥሞችና አጫጭር ታሪኮችን የያዘውን የመጀመሪያ መጽሐፏንም አሳተመች። የታተመው አንድ ሺህ ኮፒ ቢሆንም ለስዋ መጽሐፉ መታተሙ ልጅ ወልዶ እንደመሳም ያለ ትልቅ፤ በራሱ ትልቅ ደስታ የሚሰጥ ነበር።

ሥራ ፈታ በተቀመጠችበትና ምን እንደምታደርግ ግራ በገባት ወቅት በተመረቀችበት ዘርፍ ሥራ ወጣ። የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ የሚለው የሥራ መደብ ለእነሱም ተፈቀደ። ተወዳደረችና አለፈች። በዚህ መካከልም ብዙ ነገሮችን ስትሞካከር ቆይታለች። ከሞከረቻቸውና ስልጠና ከወሰደችባቸው አንዱ ኢራን ኤምባሲ የሚሰጣቸው ኮርሶች ላይ መሳተፍ ሲሆን አንዱ ኮርስ የፖለቲካል ሳይንስ ዘርፍ ያለው በኢራንና በኢትዮጵያ ግንኙነት ላይ የሚያተኩር ነበር። ሌላኛው ደግሞ ትኩረቱን የኢራን ቋንቋ ላይ ያደረገ ነው። ከዚህ በተጓዳኝ ኢምባሲው የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንድትሰራ ዕድል ይሰጣት ነበር። ሴቶችን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎችን ሰርታ አቅርባለች። ጽሑፎቹ ሴቶች በአገር ዕድገት እና በማህበራዊ ኩነቶች ላይ ያላቸው ሚና ምንድነው? እንዲሁም በሃይማኖትስ እንዴት ይደገፉና ይታያሉ? የሚሉ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ ነበሩ።

የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ ሆና በተመረቀችበት ትምህርት መስክ የመሥራት ዕድልም አግኝታለች። ይሄ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ስትይዝ የነበረባት በብዙ ሺህ የሚቆጠር የወጪ መጋራት ክፍያ እንድትከፍል ረድቷታል። ወደ እዚህ የመንግስት ተቋም ከመጣች በኋላም በአንዳንድ የራሷ የግልና በሌሎች ምክንያቶች ባትቀበለውም ከኢራን ኢምባሲ ተደጋጋሚ የጉብኝት ጥያቄዎች ቀርበውላት ነበር።

በዚህ ወቅት ጎን ለጎን በአንዳንድ የግል መገናኛ ብዙሃን ውስጥ ፕሮግራም አቅራቢ በመሆን ትሰራ ነበር። ከሰራችባቸው መካከል ከሬዲዮ "ሰላም ሀበሻ" ዛሚ ላይ ይቀርብ የነበረ የጋዜጠኛ ዘሪሁን አሰፋ፤ እንዲሁም "ፍቅርና ወንጀል" አሀዱ ሬዲዮ ላይ ይቀርብ የነበረ የጋዜጠኛ ዳዊት በቀለ ፕሮግራም፤ በተጨማሪም "የሀበሻ ኤክስፓ" ዩቲዩብ ቻናል ኤዲተር ኢን-ቺፍ ሆና የምትሰራባቸው ይጠቀሳሉ። አሁን እየሰራችበት ያለችውና ረዥም ጊዜ የቆየችበት ሰለሞን ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ከኢቢሲ ጋር የሚያቀርቡት የጋዜጠኛ ሰለሞን ጥዑመልሳን ፕሮግራም አዲስ አውቶሞቲቭ የማክሰኞው ፕሮግራም ከፍተኛ አዘጋጅና አቅራቢ የሆነችበትም ይጠቀስላታል። የራሷ ዩቲዩብ ቻናል (venufrez)ም አላት።

ወጣቷ ያሳለፈችው ውጣ ውረድ እንዲህ እንደምናወራው ቀላል አይደለም። ያሳለፈችውን ጫና ስታስታውሰው 30 ዓመት ሳይሆን 70 እና 80 ዓመት የኖረች ነው የሚመስላት። በተማረ ቤተሰብ በመወለድና በማደግ ማህል በጣም ብዙ የሚታለፉ ነገሮች እንደመኖራቸው ፍሬዘርም የነዚህ ሰለባ ሆናለች። ልክ እንደማንኛውም ሴት ሁሉ መሥራት እንደማትችል፣ ትንንሽ ነገሮችን እንድትጠብቅና ተስፋ እንድታደርግ፤ ህልሟ ትንሽ እንዲሆን እየተነገራት ነው ያደገችው። በመሆኑም በዚህ የተነሳ እጅግ ብዙ ጫና የበዛባቸውን ውጣ ውረዶች ማሳለፍ ችላለች።

ሥራ ለማግኘት በራሱ ያሳለፈችው ውጣ ውረድ ቀላል አልነበረም። የቅርብ የምትላቸውን ሰዎች አንዴ ብቻ እድሉን ስጡኝና ልሞክር ብላ እስከመለመን የደረሰችበት ነበር። ሆኖም አንዳንዶቹ ዝቅ አድርጎ የማየት፤ ሌሎቹ ደግሞ የተለየ ፍላጎት በማሳደርና አላስፈላጊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በጣም ተስፋ እንድትቆርጥና እንድታዝን አድርገዋታል። ስለ ሕይወት የተዛባና ጥሩ ያልሆነ አመለካከት እንዲኖራትም አድርገዋታል። ፍሬዘር አንዳንዴ ካገኘቻቸው ነገሮች ይልቅ ያለፈችባቸው ነገሮች ጫና ይበዛባትና "መሥራት ችያለሁ፤ እችላለሁም!!!" እንዳትል ያደርጓታል። "አልችልም እንዴ?" የሚሉ ጥርጣሬዎች እንዲፈጠሩባት ያደረጉ ሁኔታዎችንም አልፋለች።

በተጨማሪም በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዳየችው ከማገዝ፣ ከማበረታታትና እንዲህ ዓይነት ባህርይን ከማዳበር ይልቅ የአንድ ፈጣን፣ ለወጥ ያለና የተማረ ማህበረሰብ ሠራተኛ ባህርይ ነው ተብሎ የማይጠበቅ፣ ለማጥፋት ሁሉ የሚደረጉ ተግባራት ሲፈፀም መታዘብ ችላለች።

በእርግጥ ሰው ያለ እንቅፋት አልጋ በአልጋ በመሆን በተደላደለ መንገድ ላይ አይጓዝም። ሆኖም ሴቶችን ወደኋላ የሚያስቀረው ነገር በጣም ብዙ ነው። የሚያጡት ነገርም እንዲሁ ይበዛል። "እነዚህ ነገሮች አእምሮዬን ባይሰርቁኝ ኖሮ ምን አልባት የበለጠ ቦታ ላይ አልገኝና ገና ድሮ የምፈልገውን መሆን እችል አልነበር እንዴ?" ብላም ራሷን እስከ መጠየቅ ደርሳለች። ሁኔታው እጅግ ከባድና አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ማንኛውም ሰው በተለይም ሴቶች እንዲህ ዓይነቶቹን ለማሸነፍ መቆም ያለባቸው እራሳቸው እና ከራሳቸው ጋር ብቻ እንደሆነ ተምራ አልፋበታለች። «ብዙ የሚያሰናክሉና የሚያደናቅፉ ምክንያቶች አሉ» የምትለው ወጣቷ ሆኖም ምክንያቶቹ ውጤት እንደማይሆኑም ታምናለች። ብዙ ነገሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ በማመን ራስን ማዘጋጀትና ማጠንከር እንደሚገባ ምክሯን ትለማሳለች። እሷን የገጠማት የሚያስደነግጥ፣ የሚያስፈራ... ግንዛቤ ስላልነበራት አዲስ ነገርም ነበር። "እንዴት እንዲህ ይደረግና ይሆናል?" የሚለው ላይ እንጂ ወደ መፍትሄው የመምጣቱ ነገር ጊዜ ፈጅቶባታል። ዛሬም ቢሆን በጣም በጣም ወደ ኋላ እንደቀረች ይሰማታል። መድረስ ከምትፈልግበት ግማሹ ላይ እንኳን መድረስ ችያለሁ የሚል ዕምነት የላትም። ሆኖም ዛሬም የምትፈልገው ቦታ ለመድረስ የምታደርገውን ጥረት አላቋረጠችም። የምትፈልጋቸውን ነገሮች አሻግራ የምታይበት ትግል ላይ ነች። በፍፁም አላረፈችም።

ኢኮኖሚ

ባህልና ቱሪዝም

«የኢትዮጵያውያን የጋራ ባህላዊ እሴት ግንባታ ተቋም ሊመሰረት ይገባል»

- አንትሮፖሎጂስት ደስታ ሎሬንሶ

ዳግም ከበደ

ኢትዮጵያ የሺህ ዘመናት የአገረ መንግስት ታሪክ፣ ውብ ባህልና ማንነት ያላቸው ብሔረሰቦች በጋራ ተዋደውና በአንድነት ተጋምደው የሚኖሩባት አገር መሆኗ በገሃድ የሚታይ ሃቅ ነው። ሕዝቦቿ ለአይን ማራኪ፣ ጆሮ ገብና ተወዳጅ የሆኑ እሴቶች ባለቤት፤ ባህልና ወጋቸው ለባዳው የሚያስቀና ለወዳጅ ሃሴትን የሚፈጥር ጭምር ነው። ጠላትን በአንድነት መክተው ድባቅ የሚመቱ ለሉዓላዊነታቸው መከበር በጋራ ዘብ የሚቆሙ ቆራጦች ጭምር ናቸው። ሁሉም ዜጎች ኢትዮጵያዊነትን ሳይለቁና የመጡበትን ማህበረሰብ ባህልና ማንነት ሳይሸራርፉ አብረው የመኖር የሺህ ዓመታት ታሪክ ባለቤትም ናቸው። በተለያዩ ጊዜያት የእነዚህን ሕዝቦች አንድነት የሚፈታተኑ አያሌ አጋጣሚዎች ነበሩ። ይሁንና በጠንካራው አብሮነትና የተጋድሎ ወኔ ችግሮቹን በጣጥሰው በማለፍ ዛሬ ላይ ደርሰዋል።

ዛሬም ይህን መሰል አጋጣሚ በኢትዮጵያውያን ላይ የተከሰተ ይመስላል። ላለፉት 30 ዓመታት ዘርን መሰረት አድርጎ ተዋልደውና ተዛምደው የሚኖሩ ሕዝቦች መሃል ጥርጣሬንና መከፋፈልን የሚፈጥሩ አጀንዳዎች ይራገባሉ። ይሁንና የጋራ ማንነትና ያላቸው ሕዝቦች ንፋስ ያመጣውን ወጀብ ለዘመናት በገነቡት የአብሮነት ባህላዊ እሴት ለመመከት ተዘጋጅተዋል። ከሁሉም በላይ ግን የሕዝቦች የጋራ ባህላዊ እሴቶችን አሁን ካለው በእጅጉ በላቀ ማጠንከርና ማጎልበት እንደሚያስፈልግ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። ለመሆኑ "ኢትዮጵያውያን የጋራ ባህላዊ እሴቶች አሏቸው። እነርሱን ማልማትና ማጠናከር ላይ መስራት ያስፈልጋል" ሲባል ምን ማለት ይሆን?

ደስታ ሎሬንሶ በአንትሮፖሎጂ የትምህርት መስክ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን እየሰሩ ያሉና በባህል ልማትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በርካታ የጥናት ውጤቶችን ይፋ ያደረጉ ምሁር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ኢትዮጵያውያን (ብሔር ብሔረሰቦች) እምቅ የባህል ሃብት አላቸው። እነዚህ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያሏቸው የባህል እሴቶች ትልቅ ሃብት ነው። ማልማትና ማሳደግ ያስፈልጋል። ከዚህ ባሻገር ግን እንደ አገር የጋራ የሆኑና የሚያስተሳስሩ እሴቶችን ከማጎልበትና ከማበልፀግ አንፃር ብዙ ይቀራል። ይህ ባለመሆኑ ባለፉት ጊዜያት እርስ በእርስ ያለመተማመን፣ መጠላላትና አንዱ አንዱን የመግፋት ችግሮች እየተስተዋለ ነው።

"እንደ አንድ አንትሮፖሎጂስት ለአገር የትኛው ይጠቅማል የሚለውን ለማሰላሰል ስሞክር የጋራ ባህላዊ እሴቶች ላይ ለማተኮር ወስኛለሁ" የሚሉት አንትሮፖሎጂስቱ ደስታ፤ በዚህ ዘርፍ ላይ ሳይንሳዊ ምርምር በሚያደርጉበት ወቅት ኢትዮጵያውያን የጋራ የሆኑ ባህላዊ እሴቶች፣ የተሳሰረ ማንነትና አንዱ በአንደኛው ውስጥ የተጋመደ አብሮ የመኖር እሴት እንዳለው ማረጋገጥ መቻላቸውን ይጠቅሳሉ። በመሆኑን እነዚህን ባህላዊ እሴቶች ማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ።

የጋራ ባህላዊ እሴቶቻችን የትኞቹ ናቸው?

ደስታ ሎሬንሶ እንደሚገልፁት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ "የየአገራቱ የጋራ ባህላዊ እሴቶች ምን ምንድን ናቸው" በሚል በዘርፉ ምሁራን ይጠናል። ወደ ኢትዮጵያ በሚመጣበት ወቅት እጅግ በርካታ የጋራ እሴቶች ማግኘት ይቻላል። የጥናት ውጤታቸው ላይ ተመርኩዘውም በምሳሌነት "የዓድዋ ድል" መነሻ በማድረግ ብቻ ኢትዮጵያውያን በጋራ ለመሰረቷት አገር ቀናኢ፣ በሉዓላዊነታቸው ላይ የማይደራደሩና በአገር ጉዳይ በጋራ የመቆም ባህላዊ እሴት ያላቸው እንደሆኑ ያነሳሉ።

"የኢትዮጵያን በጀግንነት በአገር ላይ ጠላት ሲመጣ የሚመክቱበት እሴት በሌላው ዓለም ላይ የሌለና ብቸኛው የማንነታቸው መሰረት ነው" የሚሉት ደስታ፤ ከዚህ ባለፈ ፍቅር፣ ብሔርን ሳይሆን ሰውነትን ያስቀደመ መተሳሰብና ትብብር የኢትዮጵያውያን መገለጫና የጋራ ባህላዊ እሴት እንደሆነ ይናገራሉ። በዚያ የድል ወቅት መላው ብሔረሰቦች ልዩነታቸውን ወደጎን ትተው ከሁሉም የአገሪቷ ክፍሎች ብዙ ከሺ በላይ ኪሎ ሜትሮችን በማቋረጥ ሉዓላዊነታቸውን ያስከበሩበት ዋነኛ ምክንያትም የጋራ እሴቶች ስላሏቸው እንደሆነ ነው የሚያስረግጡት። ይህንን

«እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ የራሱም ሆነ በጥቅል የሚጋራው እሴቶች አሉት። ተነጣጥሎ የሚኖሩበት የፖለቲካ ደሴት ባለመኖሩ አእምሯቸውን ከፈት አድርገው ማስተዋልና የኢትዮጵያዊነት እሴቶችን ለማበልፀግ መትጋት ያስፈልጋል»

በወጣቱ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ማሳደግና እሴቶቹን ማጎልበት እንደሚያስፈልግ ነው የሚያስረዱት። ይህ ብቻ ሳይሆን እንደ ሌሎቹ አገራት ሁሉ መረዳዳት፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት እና ሌሎችም መሰል ማንነቶች የኢትዮጵያዊነት መገለጫና የጋራ እሴት መሆኑን ያስረዳሉ።

ከመሪዎች ምን ይጠበቃል?

"የጋራ ባህላዊ እሴቶችን ማጉላትና ማሳደግ ተገቢ ነው" የሚል ምክረ ሃሳብ በሚነሳበት ወቅት የመንግስት አመራሮችና ፖሊሲ አውጪዎች ሚና ቁልፉን ድርሻ እንደሚወስድ ይነገራል። በዚህ በኩል አንትሮፖሎጂስቱ ደስታ ሎሬንሶ ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው። በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ ግልፅ የሆነ የጋራ ባህላዊ እሴቶችን ለማበልፀግ የሚያስችል ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ተቋምም ሆነ የተደራጀ ጥናት አለመኖሩን ይገልፃሉ።

"ሁሉም ሰው ስለ ጋራ እሴት ሊያወራ ይችላል። ይሁን እንጂ ተቋማዊ በሆነ መንገድ ተጠንቶና ታትሞ ለትውልድም ሆነ ለትምህርት ተቋማት እየተላለፈ አይደለም" የሚሉት አንትሮፖሎጂስቱ ደስታ፤ በተለይ በመንግስት ስር ያሉ በባህልና በብሔር ብሔረሰቦች ጉዳይ ላይ የሚሰሩ እንደ ባህል ሚኒስትርና የፌዴሬሽን ምክር ቤትን የመሳሰሉ ተቋማት በተደራጀ መንገድ በስትራቴጂ ተደግፈው የጋራ እሴቶችን ለማጎልበት እየሰሩ እንዳልሆነ ነው የሚያምኑት። ከዚህ በመነሳትም "የኢትዮጵያውያን የጋራ ባህላዊ እሴት ግንባታና ጥናትና ምርምር ተቋም ማቋቋም ያስፈልጋል" የሚል ጠንካራ አቋም ያራምዳሉ። ይህንን ኃላፊነት መንግስት ሊወጣና በፖሊሲ፣ ህግና በተግባር መሬት ላይ የሚተረጎምበት መንገድ መፈለግ እንዳለበትም ይናገራሉ። በተለይ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚቀነቀኑ "መደመርንና" "ወንድማማችነት" የመሰሉ የጋራ እሴቶችን የሚያጎለብቱ ሃሳቦች ከቃላት ባለፈ መሬት ላይ ወርደው በጥናት፣ ፖሊሲ ተቀይረው ማህበረሰቡን ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረግ የባህል አብዮት ሊያመጡ በሚችሉበት መንገድ ላይ ሊሰራ ይገባል የሚል ጠንከር ያለ መልእክት ያስተላልፋሉ።

የጋራ እሴትና የብሔር ፖለቲካ አደረጃጀት

ከ80 በላይ ብሔርና ብሔረሰቦች ባሉበት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሶስት አስርት ዓመታት በፊት ብሔርን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ ስርዓት ተዘርግቷል። አሁንም የመንግስት የአገር መምራት ማጠንጠኛ ነው። ይህ በመሆኑ ምክንያት የጋራ ባህላዊ እሴቶችን ለማበልፀግና ጠንካራ የማህበረሰብ ትስስር ለመፍጠር አዳጋች እንደሆነ የሚናገሩ አካላት ቢኖሩም በዚህ ሃሳብ ግን አንትሮፖሎጂስቱ ደስታ ሎሬንሶ አይስማሙም። እንደ እርሳቸው እይታ ሁለቱንም በማይጋጭ መንገድ ጎን ለጎን ማስኬድ እንደሚቻል ይናገራሉ።

"የብሔር ብሔረሰቦች ሀብት የሆነው ባህል፣ ማንነት፣ ቋንቋ፣ ስነጥበብም ሆነ ኪነ ጥበብ ማደግ አለበት" የሚሉት አንትሮፖሎጂስቱ፣ የኦሮሞም ሆነ፣ የከምባታ፣ የአማራም ሆነ የሱማሌው፣ የአፋሩም ሆነ የሀረሪው ... የማንነት መገለጫዎች እንዲያድጉ በመስራት ወደ ኢኮኖሚም ሆነ የቱሪዝም ሀብትነት መቀየር ያስፈልጋል ይላሉ። እዚህ ላይ ዋነኛው ችግር የሚሆነው ግን ይህን ማንነትና ባህላዊ እሴት ወደ ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም በመውሰድ የስልጣን ማግኛና የመጫወቻ ካርድ ወደ ማድረጉ ከተለወጠ ነው። ይሄ ማድረግ ፈፅሞ ተገቢ አለመሆኑን ነው የሚያስረዱት። እያንዳንዱ ብሔረሰብ ባሉት ባህላዊ ማዕከላት ሆነ በሌሎች መሰል መንገዶች የማንነቱን መገለጫ እንዲያለማ መደረግ አለበት። ይሁንና የጋራና የአንድነት መሰረት የሆኑት ባህላዊ እሴቶችን ደግሞ በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ በተመሳሳይ ያለምንም ተቃርኖ ኮትኩቶ ማሳደግ እንደሚቻል ይገልፃሉ። ይሁንና የብሔር ብሔረሰቦችን ባህልና የማንነት መገለጫዎች ለፖለቲካ ስልጣን ማግኛ መንገድ ወደላይ አምጥቶ መጠቀም የጋራ እሴቶች ግንባታ ላይ ተፅዕኖ እንደሚፈጥር ያብራራሉ።

"እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ የራሱም ሆነ በጥቅል የሚጋራው እሴቶች አሉት። ተነጣጥሎ የሚኖሩበት የፖለቲካ ደሴት ባለመኖሩ አእምሯቸውን ከፈት አድርገው ማስተዋልና የኢትዮጵያዊነት እሴቶችን ለማበልፀግ መትጋት ያስፈልጋል" የሚል ምክረ ሃሳብ ይሰጣሉ። በተለይ የአንድን ማህበረሰብ የፍትህ፣ የእኩልነት እና መሰል ማህበራዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች የሚፈታበት መንገድ መቀየስ እንጂ ማንነት ላይ መሰረት ያደረገ ፖለቲካ በማቀንቀን የስልጣን ጋሻ ማድረግ "የጋራ እሴቶቻችንን" የሚሸረሽርና ለግጭትና የሚዳርግ ነው ሲሉ ይናገራሉ ።

መውጫ ምክረ ሃሳብ

በመግቢያችን ላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ኢትዮጵያውያን ጠላትን በጋራ ድባቅ መትተው ሉዓላዊነትን ከማስከበር ጀምሮ በደስታም ሆነ በሃዘን አብሮ የመኖር፣ የመተባበር፣ የመረዳዳትና የፍቅር እሴቶችን ለዘመናት አዳብረው በአንድነት የኖሩ ሕዝቦች ናቸው። ይህን ልዩ ሃብታቸውን ደግሞ አሁንም ይበልጥ ባሳደግ የገጠማቸውን የውስጥም ሆነ የውጭ ፈተናዎች መጋፈጥ ይኖርባቸዋል።

አንትሮፖሎጂስቱ ደስታ ሎሬንሶም በዚህ ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ ይስማማሉ። በጉዳዩ ላይ ሳይንሳዊ ጥናት በመስራትም ከላይ ካነሱት የጉዳዩ ዋንኛ ማጠንጠኛዎች በተጨማሪ የሚከተለውን ጥቅል መደምደሚያ በምክረ ሃሳብ ሰንዝረው ሃሳባቸውን ይቋጫሉ።

እንደ አንትሮፖሎጂስቱ የጥናት ውጤት ጥቅል ሃሳብ "በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያዊነት ፈተና ላይ ነው" በማለት የጋራ ባህላዊ እሴቶች ከተዳከሙ መሆኑን ያስረዳሉ። የጋራ ባህላዊ እሴቶችና አገር ግንባታ የሚነጣጠሉ አለመሆናቸውንም ይጠቁማሉ፡፡ ኢትዮጵያ እና የአገሪቱ ታሪክ የተገነባው በጋራ ባህላዊ እሴቶች መሆኑንም በማስረጃነት ያስቀምጣሉ፡፡ አሁን አገሪቷ ከደረሰችበት የፖለቲካ፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲሁም ለውጥ አኳያ በጋራ ባህላዊ እሴቶቻችን ላይ መስራት ለብልጽግና እና መደመር መርሆዎች መሳካት ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረውም ይናገራሉ፡፡

"በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሁሉም ሕዝቦች ወይም ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የየራሳቸው ማንነት፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክ ያላቸው ናቸው" በማለትም እነዚህን ማንነቶች በግል ወይም በተናጠል ማሳደግ ወይም በትይዩ (parallel) የጋራ እሴቶቻችን ማስተሳሰር፣ መገንባት እና ኢትዮጵያዊ ማንነትን ማጠናከር ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ኢትዮጵያዊ ማንነት ወይም አገራዊ አንድነት እና ሉዓላዊነት የወቅቱ ትልቁ የአገሪቱ አጀንዳ መሆኑንም ያነሳሉ፡፡ በዚህ አገራዊ ማንነት ላይ መሰረት ጥለን የኢኮኖሚ ዕድገት እና ብልጽግና በተባበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማረጋገጥ ይቻላል ይላሉ፡፡

"የጋራ ባህላዊ ትስስር የኢኮኖሚ ማህበራዊ ትስስር፣ የፖለቲካ መረጋጋት፣ ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ ዋስትና ይሰጣል" የሚሉት አንትሮፖሎጂስቱ፤ ከዚህም በተጨማሪ የኢኮኖሚ መስተጋብር እና የንግድ ልውውጥ (shared values) እንደሚፈጥር ያስገነዝባሉ፡፡ ጠንካራ አገር በጋራ እሴት ውስጥ እንደሚገነባም እንደዚያው ያስረዳሉ፡፡

በዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሳይንሳዊ ምርምር እንዳደረገ ምሁር፤ ሕዝቦች ወንድማማችነትን የሚያጎለብቱት የጋራ እሴቶቻቸውን ለይተው ትኩረት ሲሰጡት መሆኑን ነው የሚያምኑት፡፡ የአገር ውስጥ ማህበራዊ ትስስር እና የጋራ እሴቶች ሲላሉ ለእርስ በእርስ ግጭት (civil war) መነሻ እንደሚሆን ይገልፃሉ፡፡ ይህ እሴት የማይዳብር ከሆነ ሕዝቦች አገርን አናውቅም፣ ትስስር የለንም ማለታቸው እንደማይቀር ነው የሚያስረዱት፡፡ በዚህ ምክንያትም ጥላቻ ይሰፍናል፣ ኢኮኖሚ ይወድማል፣ የአገር ጸጥታ ይናጋል፡፡ ሕዝቦች በስጋት ይኖራሉ፣ የሕዝቦች ጥርጣሬ እና አለመተማመን ጎልቶ ይወጣል፡፡ የጋራ ባህላዊ እሴት መገንባት አገሪቷን ቀደምት ታሪኮች የጀግንነት፣ የሉዓላዊነት፣ የመተባበር፣ የመረዳዳት እሴቶች ዕውቅና መስጠት ነው፡፡ ኢትዮጵያ አንድ አገር ደግሞም የብዙ ሕዝቦች የጀግንነት እና ሉዓላዊነት ውጤት ነች በማለት ሃሳባቸውን አካፍለውናል ።

ስፖርት እና መዝናኛ

ሳምንቱን በታሪክ

የአጼ ቴዎድሮስ የመቅደላ ስንብት

ዋስልኝ አየለ

ዘመነ መሳፍንት በብዙ አጋጣሚዎች ይጠቀሳል፡፡ የየአካባቢው የጎበዝ አለቆች የበዙበትና አገር የተበታተነችበት ዘመን ነበር፡፡ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪክ ስማቸው ደምቆ የታየው ያቺን የተበታተነች ኢትዮጵያ አንድ በማድረጋቸው ነው፡፡ ዘመነ መሳፍንትን አንኮታኩተው ኢትዮጵያን አንድ አደረጉ፡፡

እኚህ ጀግና በዚህ ሳምንት ይታወሳሉ፡፡ ለኢትዮጵያ አንድነትና ዘመናዊነት ቆራጥ አቋምና ወኔ የነበራቸው ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የፋሲካ ማግሥት መቅደላ አምባ ላይ ከእንግሊዞች ጋር ውጊያ ገጥመው ድሉ የእንግሊዞች ሲሆንና እጃቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ አሻፈረኝ ብለው ራሳቸውን የሰውት በዚህ ሳምንት ሚያዚያ 6 ቀን 1860 ዓ.ም መሆኑም ዛሬ በሳምንቱ በታሪኩ አምዳችን እንድናስታውሳቸው አድርጎናል፡፡

የአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት እና በሎርድ ኔፒዬር የተመራው የእንግሊዝ ሠራዊት ጦርነት ገጥመው ድሉ የእንግሊዞች ሲሆን፣ አፄ ቴዎድሮስ በእንግሊዞች እጅ ከመውደቅ ራሳቸውን ማጥፋትን መርጠው ሽጉጣቸውን ጠጥተው ሞቱ፡፡ ቀብራቸውም በመቅደላ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ፡፡ እኛም የዚህን ጀግና ታሪክና ሥራዎች እናስታውሳለን፡፡

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የጀግና ምሳሌ፣ የቆራጥነትና ወኔ ማሳያ ናቸው፡፡ ስለጀግንነትና ቆራጥነት ሲነሳ በአጼ ቴዎድሮስ ይመሰላል፡፡

የታሪክ ባለሙያዎችና ምሁራን የሚሉት አንድ ነገር አለ። አጼ ቴዎድሮስ የጦር ጀግና ብቻ አልነበሩም። ዘመናዊነትንና ሥልጣኔን የሚመኙ ባለራዕይ ነበሩ፡፡ ለዚህም የደበረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ጋፋት ኢንዱስትሪ በሚል የቴክኖሎጂ ንቅናቄ ጀምሯል፡፡ በየጊዜው ውይይቶችንም ያዘጋጃል። ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው አንድ የውይይት መድረክ ላይ ተሳታፊ ነበርኩ፡፡ ብዙ ምሁራን ሲያነሱ የሰማሁትም አጼ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ራዕይ የነበራቸው መሆኑን ነው፡፡ ንባብና ሥልጣኔን ያስተዋውቁ ነበር፡፡ አብዛኛው ታሪካቸው ግን የሚታወቀው ከጦር ጀግንነት ጋር የተያያዘው ነው፡፡

ስለ አጼ ቴዎድሮስ የታሪክ ጸሐፊዎችና ተመራማሪዎች በተለያየ ጊዜ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ እነዚህ የታሪክ ጸሐፊዎች የአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆኑ የውጭ አገራት ጸሐፊዎች ጭምር ናቸው፡፡ ጥቂቶችን መጠቃቀስ እንችላለን።

ፕሮፌሰር ዶናልድ ክሬሚ

«ቴዎድሮስ የዘመናዊ ሥልጣኔ ሐሳብ የገባው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር።»

ቫልድማየር፡

«ቴዎድሮስ፣ ኃይልና ታላቅነት ሳያንሰው፣ የምኞትና የቅምጥል ኑሮ የማያታልለው እንዲህ ያለ ንጉሥ ከቶ የት ይገኛል? የሁላችንም እምነት እግዚአብሔር ኃይሉን የለገሠው የሕዝቡንም ቁሣዊና መንፈሣዊ ደኅንነት ለማረጋገጥ የታጨ መሣሪያ መሆኑ ነው።»

በፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ የታሪክ መጽሐፍ ላይ እንደሰፈረው፤ መረጃ ቴዎድሮስ ለአገራቸው ዕውቀት መስፋፋት የነበራቸውን ጉጉት ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ፡-



(1) ጥር 1858፣«የኢትዮጵያ ሰዎች ድንቁርነታችን ዕውርነታችን ሳይሰሙት አይቀርም።»

(2) መጋቢት 1858፣ « አሁንም እኔ የምፈልገው ዕውር ነኝና ዓይኔ እንዲበራ ጥበብ ነው።»

(3) ሚያዝያ 1858፣ « የኢትዮጵያ ሰዎች ዕውር ነኝ፤ ዓይናችንን ያበሩልን ፤ እግዚአብሔር በሰማይ ያብራሉዎ!»

(4) ሚያዝያ 1859፣ «ከብት አለመፈለጌ ክብር ሆኜ አይደለም፤ ዕውር አህያ ነኝና ለጥበብ ዓይኔን ትከፍቱልኝ ብየ ነው እንጂ፣ በእግዚአብሔር ኃይል፤» ብለዋል፡፡

ከእነዚህ ደብዳቤዎች አንድ ነገር እንረዳለን፡፡ ይኸውም አጼ ቴዎድሮስ ለእውቀት ሽግግር የነበራቸውን ከፍተኛ ፍላጎት። ለአገሪቱ ዘመናዊነት ያደረጉት ጥረት እዚህ ላይ ግልጽ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለእርሳቸው የተጻፉ አንዳንድ መጻሕፍት እንዳሰፈሩትም አጼ ቴዎድሮስ ከራሳቸው በላይ ለሌላው ያስባሉ፡፡ የግል ሕይወታቸው አያሳስባቸውም። ከአገር ውስጥ የታሪክ ጸሐፊዎችም ተከለጻድቅ መኩሪያ « ቴዎድሮስ፣ ሞትን የናቁ፣ ድሎትን የራቁ» ናቸው ሲሉ ገልጸዋቸዋል።

በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ታስረው ከነበሩት እንግሊዛውያን ውስጥ አንዱ የነበረው ዶክተር ሐንሪ ብላንክ ስለአፄ ቴዎድሮስ «ለመጀመሪያ ጊዜ በ1852 ዓ.ም አፄ ቴዎድሮስን ሳገኛቸው ዕድሜያቸው 48 ይሆን ነበር! በሰላም ጊዜ ለስላሳ ሆነው ደስ የሚያሰኙ በተቆጡ ጊዜ ደግሞ በርበሬ መስለው የሚያስደነግጡና የሚያሹበሩ እሳተ ገሞራ የሚወረውሩ ነበሩ! በድንገት ሲቆጡ መላ አካላቸው የሰውን ልጅ ከፍ ካለ ድንጋጤ ላይ ይጥላል! ጠይሙ ገላቸው ሲኮሰኩስ ..ስሱ ከንፈራቸው ሲንቀሳቀስና ፀጉራቸው ሲዘናፈል በጠቅላላ ሰውነታቸው የአንበሳነት ፀባይ የያዘ አስደንጋጭ ይሆናል!» ብሏል፡፡

አፄ ቴዎድሮስ የንግሥና ስያሜ ያቸው ቴዎድሮስ እንዲሆን የመረጡት «ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ሲነግስ ኢትዮጵያን እስከ ባህር ያሰፋታል፤ ፍርድና አስተዳደርንም ያስተካክላል» የሚባል ትንቢት ስለነበር ሕዝቡ «ይህ ትንቢት የእርስዎ ነው» እያሉ አሞካሿቸው። «ስሜን ቴዎድሮስ በሉ» ብለው እንዳወጁ ታሪካቸውን ጽፎ በ1985 ያሳተመው ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ ይነግረናል፡፡

ጳውሎስ «ቴዎድሮስ እንዴት ያሉ ሰው ነበሩ?» የሚለውን ጥያቄ በመፅሐፉ አንስቶ «ሁሉንም ፀባይ አሟልተው የያዙ ሰው ነበሩ። ይህም ማለት ደግ ናቸው፣ ክፉም ናቸው፣ ሩህሩህ ናቸው፣ ጨካኝም ናቸው፣ ፍርድ አዋቂ ናቸው፣ ፍርድ ገምድልም ናቸው» ሲል ማስረጃ እያጣቀሰ ይገልፃ ቸዋል።

እስኪ የአፄ ቴዎድሮስን ፍርዶች እንመለከትና በዘመኑ የነበረውን የፍትህ ስርዓት በመጠኑ እንቃኝ። አጼ ቴዎድሮስ በሰጧቸው ፍርዶች መነሻነትም በትንቢት ተነግሮላቸዋል። እንደተባለው ፍርድና አስተዳደርን በማስተካከል ረገድ ምን ያህል ተሳክቶላቸው ነበር የሚለውን የራሳችንን ግንዛቤ እንይዛለን። ፍርዶቹ አንዳንዶቹ አስገራሚ፣ አንዳንዶቹ አሳዛኝና አስደንጋጭ አንዳንዶቹም አስተማሪ ናቸው።

የጋይንቱ ችሎት

አፄ ቴዎድሮስ ጎንደር ጋይንት ላይ ሰፍረው ሰለ ወታደሮቻቸው በአርሶ አደሩ ላይ «ተሰሪ» አገቡአቸው። ተሰሪ ማግባት ማለት አርሶ አደሩ ወታደሮቹን እንዲቀልብ በየቤቱ መመደብ ማለት ነው። በወቅቱ የተደራጀ ጦር ሰራዊትና ለጦር ሰራዊቱ የሚመደብ የመንግሥት ባጀት ስላልነበር የነጋስታቱ ጦር በየደረሰበት ያለው ሕዝብ እንዲቀልበው ይታዘዝ ነበር። ከእነኚህ የጋይንት እና የአካባቢው አርሶ አደር እንዲቀልባቸው ከታዘዘላቸው የቴዎድሮስ ወታደሮች መሀል አንዱ ወታደር አንዱን አርሶ አደር ገደለው። የሟች ዘመዶች ለአፄ ቴዎድሮስ አመለከቱ። አፄውም ወታደሮቻቸውን አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን እንዲጠቁሙ አዘዙ። ሆኖም ወታደሮቹ በሙሉ በአንድ ላይ አድመው ገዳዩን አናውቅም ብለው በቁስ እየተገዘቱ ስለወጡ ገዳዩ ሊታወቅ አልቻለም።

ቴዎድሮስ ገዳዩን ወታደር ለማወቅ የተደረገው ሙከራ ባለመሳካቱ ተናደው «ወታደር ብላ! ባላገር አብላ! ያልኩ እኔ ነኝ። ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል» ብለው ተነስተው ለከሳሽ ነገሩት። ከሳሽም ምኑ ሞኝ «እኔ ንጉስ መግደል አይቻለኝም» አለ። ቴዎድሮስ እንግዲያውስ ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም ብለው ለሟች ወገኖች የደም ካሳ ገንዘብ ከፍለው አሰናበቷቸው።

የንጉሱ ትዕዛዝ

ቴዎድሮስ ለአንድ ታማኝ ወታደራቸው ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላልፈው «በፈርቃ በር በኩል እርጉዝ ሴት እንኳን ብትሆን እንዳታልፍ ጠንከረህ ጠብቅ» አሉት።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ሌላውን ወታደራቸውን ጠርተው «ፈረስ እያለዋወጥክ ይህን ወረቀት የጁ አድርሰህ በስድስት ቀን ውስጥ በአስቸኳይ ተመለስ» ብለው አዘዙ። መልክተኛው ወታደር መልዕክቱን ለማድረስ ፈርቃ በር በሚባለው ቦታ ማለፍ ግድ ሆነበት። ፈረሱን እየጋለበ ፈርቃ በር ደረሰ። አስቀድሞ ማንንም እንዳያሳልፍ የታዘዘው የፈርቃ በር ዘበኛም የንጉሱን መልዕክት እንዳያልፍ ከለከለው።

መልዕክተኛው «ከንጉሡ በስድስት ቀን የጁ ደርሼ እንድመለስ በአስቸኳይ ተልኬ ነው ልለፍ» አለው።

የፈርቃ በር ጠባቂም «ከንጉሥ ከተላከ አትከልክሉት ይለፍ የሚል በማህተም የተደገፈ የይለፍ ደብዳቤ ካለህ አሳየኝ እና አሳልፍሃለሁ ካልሆነ ግን እኔም የንጉሥ ትዕዛዝ ስላለብኝ አታልፊም» ሲል መለሰለት።

መልዕክተኛው ወታደርም የንጉሥ ትዕዛዝ ሆኖበት በግድ አልፋለሁ ብሎ መንገድ ሲጀምር ጠባቂው ወታደር በጥይት ተኩሶ ገደለው።

የሟቹ መልዕክተኛ ወገኖችም ጉዳዩን ከሰሱና ለፍርድ አፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ። በችሎት የተቀመጡት ፈራጆች ሁሉ ጉዳይ ላይ ፈረዱ «እምቢ አልፋለሁ ቢልህ ለንጉሥ ማመልከት ሲኖርብህ እንዴት የንጉሥ መልዕክተኛ ትገላለህ! ለጥፋትህ ሞት ይገባሃል» ሲሉ ፈረዱበት።

አንድ አስተዋይ ፈራጅ ከተቀመጡበት ተነስተው «መታየት የሚገባው ከንጉሡ የተሰጠው ትዕዛዝ ነው። ንጉሡ የፈርቃ በር ጠባቂን ጠርተው ያለኔ ፈቃድ እርጉዝ ሴት እንኳን እንዳታልፍ ብለው አዘዙ። መልዕክተኛውን ደግሞ በአስቸኳይ የጁ ደርሶ እንዲመጣ በማዘዛቸው በዚያ በፈርቃ በር በኩል ማለፍ ነበረበት። ስለዚህ ጥፋቱ የሚመለከተው ንጉሡ ነገስቱን ነው። ነገር ግን ብርሃን ናቸውና ምን ይደረግ» ብለው ተቀመጡ።

እዚህ ጋር እንግዲህ በዚያ ዘመን የነበረውን ንጉሥ የሚያስተቸ ዲሞክራሲ ሳናደንቅ አናልፍም። የአስተዋዩ ፈራጅ ንግግር ብቻ ሳይሆን የንጉሡም ምላሽ የሚደንቅ ነው።

አፄው ምን አሉ መሰላችሁ! ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው «እንዲህ ነው መሸምገል፣ ሁለት ፀጉር ማብቀል» ብለው የአስተዋዩን ፈራጅ ፍርድ ካደነቁ በኋላ «በደለኛው እኔ ነኝ ፍረዱብኝ» ብለው በተከሳሹ ወታደር ቦታ ወርደው ቆሙ። ከዛም ፈራጆች በሰጡት ፍርድ መሰረት ለሟች ወገኖች 500 ብር የደም ካሳ እንዲከፍሉ አፄ ቴዎድሮስ ላይ ፈረዱና ጉዳዩ በዚህ ተቋጨ።

የአጼ ቴዎድሮስ ነገር ጳውሎስ ኞኞ እንዳለው ነው፡፡ ደግ ናቸው፣ ክፉም ናቸው፣ ሩህሩህ ናቸው፣ ጨካኝም ናቸው፡፡ ከወኔ እና ጀግንነታቸው በተጨማሪ ለሥልጣኔና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ጥረት ያላቸው ባለራዕይ ነበሩ፡፡ እኚህን ጀግና እነሆ ታሪክ ሲያወድሳቸው ይኖራል!

የኮሪያ ዘማች

ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን/ ቴዲ አፍሮ / ስለ ኮሪያ ዘማቾች በሰራው ዜማ

ሄዶ ከኮሪያ ዘማች ሲመለስ

ያወሳል ናፍቆቱን በክራሩ ድምጽ ማለቱ ይታወቃል። የዚህ ሳምንት ሌላኛው ትውስታ ባለክራሩን የሙዚቃ አርበኛ ካሳ ተሰማን አስከትሎ ወደ ኮሪያ የሄደው የኢትዮጵያ አርበኞች ታሪክ ነው፡፡

ሚያዚያ 8 ቀን 1943 ዓ.ም 2 ሺህ 168 ወታደር ያሰለፈው የኢትዮጵያ የክቡር ዘበኛ ሠራዊት፣ ቃኘው የሻለቃ ጦር ወደ ኮሪያ ዘመተ። ከዘማቾቹ መካከል አንዱ የነበረው «የክራሩ ጌታ» 50 አለቃ ካሣ ተሰማ ይገኝበታል። «እልም አለ ባቡሩ» በሚለው ዘፈኑም ክስተቱን ለታሪክ አስቀምጦታል፡፡

የመጀመሪያው ዙር የኮሪያ ዘማቾች አንድ ሺህ 153 ሲሆኑ ቀኑ ግን በትክክል አልተገለጸም፡፡ አብዛኞቹ መረጃዎች የሚያሳዩት በመጋቢት ወር መጨረሻ አካባቢ መሆኑን ነው። የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከሦስት ዓመት በፊት በሰራው ዘገባ መጋቢት 30 የሚል አለው፡፡ ምናልባት እሱ የመጀመሪያው ከሆነ የሚያዚያ ስምንቱ ሁለተኛው ዙር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ የኮሪያ ዘማቾች በዚህ ሳምንት ይታወሳሉ ማለት ነው።

የኮሪያ ዘማች እና ከኮሪያ ዘማቾች ማህበር መሥራች አንዱ የሆኑት የማህበሩ ፕሬዚዳንት ኮሎኔል መለሰ ተሰማ በተመሳሳይ ከዘማቾች አንዱ የሆኑት አስር አለቃ ዘነበወርቅ በላይነህ የኮሪያ ዘማቾች 60ኛ ዓመት ሲከበር ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገው ነበር፡፡

ዘማቾቹ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ዘመቻው በአምስት ዙር ነበር የተፈጸመው፡፡ በአጠቃላይ ከስድስት ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የዘመቱ ሲሆን 122 የሚሆኑት ተሰውተዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ወታደሮች አንድም የተማረከ አልነበረም፤ «ሬሳ እንኳን አልተማረከብንም» ይላሉ ዘማቾቹ።

በ2005 ዓ.ም የኮሪያ ጦርነት 60ኛ ዓመት ሲዘከር ቢቢሲ ዓለም አቀፍ «ኢትዮጵያዊው ጀግና በኮሪያ ጦርነት» በሚል ርዕስ የኮሪያ ዘማች ስለነበሩት ሌተናል ማሞ ሀብተወልድ ሰፊ ሐተታ አስነብቧል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት ለዓለም አሳውቋል፡፡ የቢቢሲ ዓለም አቀፍ ሐተታ የመግቢያው ጽሑፍ ደመቅ(Bold) ተደርጎ እንዲህ ተጽፏል፡፡

«ከ60 ዓመታት በፊት፤ ኢትዮጵያ ጦርነት ላይ ነበረች። ጦርነት አፍሪካ ውስጥ እንዳይመስላችሁ! ይልቁንም በሺዎች የሚቆጠር ማይል ርቀት ላይ ኮሪያ ውስጥ ነው...» እያለ ይቀጥላል፡፡

ቢቢሲ በዚያው ሐተታው እንደገለጸው፤ ኢትዮጵያውያን በኮሪያ 253 ውጊያዎችን (battles) አድርገዋል፡፡ «በጦር ሜዳ እጅ አንሰጥም!» የሚል መሪ ቃል ነበራቸው፡፡ መሪ ቃላቸውንም በተግባር አሳይተዋል።

የቃኘው ሻለቃ ጦር በተባበሩት መንግስት ሰላም አስከባሪ ኃይል ውስጥ በመሆን በኮሪያ አኩሪ ገድል ፈጽሟል፤

እነሆ ኢትዮጵያም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለምም ሰላም በማስከበር እንድትታወቅ አደረጋት፡፡ እነዚህ የኮሪያ ዘማች ጀግኖችም ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡

የዓለም ሰላም አስከባሪነታቸው ከዚያም በኋላ ቀጥሏል። በኮንጎና በርዋንዳም ታሪክ ሰርተዋል፡፡ በሱዳን ዳርፉር፣ በሱዳንና ደቡብ ሱዳን አወዛጋቢ አካባቢ አብዬ ግዛት፣ በሶማሊያም እንደዚያው፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

የዝነኞች ገጽ

ተሾመ ምትኩ - የዘመናዊ ሙዚቃችን አባት

(አቤል ገ/ኪዳን)

የዘመናዊ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ የሚታይ አሻራ ካላቸው አካላት መካከል ዋነኛው በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የግል ባንድ የሆነው ሶል ኤኮስ ባንድ ነው። ይህ ባንድ በኦርኬስትራዎች ብቻ የተዋቀረውን የኢትዮጵያ የሙዚቃ መልክአ ምድር ሰብሮ የገባ የግል ባንዶች በኩር ሲሆን፣ ለዝነኞቹ ሮሀ እና አይቤክስ ባንድም ወላጅ ነው።

የዚህ ባንድ መስራች ደግሞ ታላቁ ሙዚቀኛ ተሾመ ምትኩ ነው። በዛሬው የዝነኞች ገጽ አምዳችን ከአገር ከወጣ ግማሽ ክፍለ ዘመን ገደማ የቀረበውን ይህን ግዙፍ የሙዚቃ ሰው እንዳስሳለን። ይህንንም በተለያዩ ጊዜያት ያደረጋቸውን ቃለመጠይቆች አሰባስበን እንደሚከተለው ታሪኩን በአጭሩ ጽፈናል።

ከዚያ በፊት ግን አንባቢ ተሾመ ምትኩ ማን ነው ብሎ ግራ እንዳይጋባ ዛሬም ድረስ እንደ አዲስ እየተደመጡ እና እየተዘፈኑ ካሉ ሙዚቃዎቹ ጥቂቶቹን እናስታውስ፤- ጋራ ስር ነው ቤትሽ ፤ ሞት አደላድሎኝ ፤ ሀሳቤ ፤ ሱሰኛሽ ፤ የመቃብር እጮኛዬ ፤ ቼ በለው ከሙዚቃዎቹ መካከል ይጠቀሳሉ።

ተሾመ የተወለደው እዚህ አዲስ አበባ ቀበና አካባቢ ነው። ወቅቱም በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1942 ዓ.ም ገደማ ነው። ስወለድ ጀምሮ ነው ከሙዚቃ ጋር በፍቅር የወደቅኩት የሚለው ተሾመ፣ ስለ እድሜ ልክ ወዳጁ ስለሙዚቃ ሲያወራም ሆነ ተወዳጅ ሙዚቃዎቹን ሲጫወት በጥልቅ ስሜት ውስጥ ሆኖ ነው።

የሙዚቃ ፍቅሩን የጀመረው ከእናቱ ድምጽ በመስማት ይመስላል። የተሾመ እናት እንደ ብዙሀኑ የኢትዮጵያ እናቶች ስራ እየሰሩ ለስለስ ያለ ልብ የሚነካ እንጉርጉሮ የሚንጎራጉሩ ሲሆን፣ የተሾመ ጆሮም የተቃኘው በዚያ ነው።

ሙዚቃን መጫወት የጀመረው ገና የዐ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት ነው። በዚያን ወቅት ዐ ክፍል የሚባል የነበረ ሲሆን፣ እዚያ ክፍል ላይ ለትምህርት መሰረታዊ የሆኑትን እንደ ፊደል መቁጠር ያሉ ነገሮች ተምሮ ያለፈ ብቻ ነበር አንደኛ ክፍል የሚገባው።

ተሾመ ከዐ ክፍሉ በፊት ቄስ ትምህርት ቤት ገብቶ ፊደል ቆጥሮ ዳዊት የደገመ ስለነበረ ኮከበ ጽባህ ገብቶ ዐ ክፍልን ሲማር አልከበደውም፤ ተማረ። ትምህርት ቤት ሲሄድ ግን ብዙ ጊዜ አርፋጅ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ጠዋት ከእንቅልፉ እንደተነሳ በሬዲዮ ሙዚቃ እየሰማ ብዙ ደቂቃዎችን ስለሚያልፍ ነው። የሙዚቃ ፍቅሩ በዚያ ልክ ነበር። በተለይም ክራር እና በገና ያለባቸው ሙዚቃዎችን በጣም ይወድድ ነበር። አንዳንዴ እንደውም ዋሽንት የሚጫወት ሰው ካየ ትምህርት ቤቱን እርግፍ አድርጎ ቁጭ ብሎ ሊሰማ ሁሉ ይችላል።

ዐ ክፍልን ጨርሶ አንደኛ ክፍል ሲገባ በሚማርበት ትምህርት ቤት የሙዚቃ ትምህርት ተጀመረ። የሙዚቃ መምህሩ ደግሞ ዴንማርካዊው ፖል ባንክ ሀንሰን ናቸው። መምህሩ ተማሪዎችን የሙዚቃ ምት አጠባበቅ፤ አዚያዚያም ወዘተ ላይ ስልጠና ይሰጣሉ። ከዚያም ይፈተናሉ። ተሾመም ተፈተነ ፤ አለፈ። መምህሩ ያቋቋሙት የሙዚቃ ቡድን አባል ሆነ። ከእሱ ጋር በኋላ ላይ ሶል ኤኮስን ያቋቋሙት ወንድሙ ቴዎድሮስ ምትኩ ፤ ተስፋዬ መኮንን እና ታምራት ፈረጃም የቡድኑ አባል ሆኑ።

ሙዚቃ አፍቃሪው ተሾመ ከመምህሩ ሚስተር ሀንሰን ቤት አንድ የተለየ ድምጽ የሚያወጣ የሙዚቃ መሳሪያ የመምህሩ ባለቤት ሚስስ ማርጋሬት ሲጫወቱ አየ። የሙዚቃ መሳሪያው ፒያኖ ነው። በድፍረት እንዲያስተምሩት ጠየቃቸው። ወይዘሮዋ ተገረሙ። ግን ፈቃደኛነታቸውን ገለጹለት። እሺ አስተምርሃለሁ፤ ግን አንድ ነገር ቃል መግባት አለብህ። በየቀኑ ከ10 እስከ 11 ሰዓት ሳታረፍድ ሳትቀር መምጣት አለብህ አሉት፤ ተስማማ።

ትምህርቱ ተጀመረ። ወ/ሮ ማርጋሬት ለአዲሱ ተማሪያቸው ከረሜላ ፤ ብስኩት ፤ ለስላሳ እየጋበዙ ያስተምሩት ጀመር። በፒያኖ የተጀመረው ትምህርት ትራምፔት ቫዮሊን እና ድራምንም ጨመረ።

ተሾመ ሙዚቀኛ ሆነ። አባቱ አቶ ምትኩ ልጃቸው ሙዚቃ መማሩ ባይከፋቸውም ነገር ግን ከመሳሪያዎች ሁሉ ግን ትራምፔትን አልወደዱትም። ምክንያታቸው ደግሞ በልጃቸው ሳንባ ላይ ጉዳት ያመጣል ብለው ማሰባቸው ነው። ቢሆንም ተሾመን ማስቆም አልቻሉም። በየቀኑ ጠዋት 12 ሰዓት ተነስቶ የመጀመሪያ ስራው ትራምፔትን መጫወቱን ተያያዘው። ጎረቤትም የሚነቃው በተሾመ ትራምፔት ድምጽ ነው። ከዚያም 1 ሰዓት ሲል ትምህርት ቤት ደርሶ ሰንደቅ አላማውን ይሰቅላል። ማታም እንደዚሁ የሰቀለውን ሰንደቅ አውርዶ ይመለሳል።

እንዲህ እንዲህ እያለ ያደገው የሙዚቃ ሕይወት ቀጣዩ ደረጃ ባንድ መመስረት ሆነ። ተሾመን ፤ ወንድሙን ቴዎድሮስ ፤ ታምራት ፈረጃ ፤ ተስፋዬ መኮንንን እንዲሁም በኋላ ላይ ተወዳጁን ድምጻዊ ሰይፉ ዮሀንስን እና ጊታር ተጫዋቹን አሉላ ዮሀንስን የያዘው ሶል ኤኮስ ባንድ ተመሰረተ።

ሶል ኤኮስ በወቅቱ ካሉት የቴአትር ቤት ኦርኬስትራዎች ውጭ የሆነ የመጀመሪያው ባንድ ሲሆን አጨዋወቱም ለየት ያለ ነበር። ተሾመ በግሉ «ሸግዬ ሸግዬ ሸግዬ ሸጊቴ» በሚለው ሙዚቃው የምናውቀው የአሰፋ አባተ ተጽእኖ እንዳለበት የሚናገር ሲሆን፣ ባንዱ ደግሞ በወቅቱ በጣም ተወዳጅ የነበሩት ጥቁር አሜሪካዊ ድምጻውያን ጀምስ ብራውን ፤ ማርቪን ጌይ ፤ አሪታ ፍራንክሊን እና ሌሎች ተጽእኖ ያለበት ነበር። ኢትዮጵያዊውን ሙዚቃ ከነዚህ ድምጻውያን የአጨዋወት ስልት ጋር እያዳቀሉ ነበር እንደ ጋራ ስር ነው ቤትሽ እና መሰል ለየት ያሉ ተወዳጅ ሙዚቃዎች የሰሩት።

የተሾመ እና የሶል ኤኮስ ባንድ ዝና መናኘት ጀመረ። እነሱ ይገኙበታል የተባለ ቦታ ሁሉ በታዳሚ መሞላት ጀመረ። በተለይም ወጣቱ በጣሙን ወደዳቸው። እነሱ ተወዳጅ የሆኑበት ያ ወቅት ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ አገር ፖለቲካዊ ውጥረት ውስጥ የነበረችበት ወቅት ነበር።

ዘውዳዊ ስርአቱን ለመገርሰስ በተማሪዎች የሚመራው እንቅስቃሴ ተጧጡፏል። ወጣቱ በተለይም የሁለተኛ ደረጃ እና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአንድ ጎን የለውጥ ሀይሎች በሌላ ጎን የነተሾመ ሙዚቃ አድናቂዎች ነበሩ።

አንድ ቀን እነ ተሾመ በሺ የሚቆጠር ተማሪ በታደመበት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልደት አዳራሽ ሙዚቃ ሊያቀርቡ ተገኙ። ሰይፉ ዮሀንስ ሶስት ሙዚቃዎችን አቅርቦ ወረደ። ተረኛው ተሾመ ነው። ወደ መድረክ ሲወጣ ተማሪው በሙሉ «ፋኖ ተሰማራን » ካልዘፈንክልን ብሎ አስጨነቀው። በተማሪው ዙሪያ ክቡር ዘበኛ እና ፖሊስ መሳሪያቸውን ታጥቀው ተኮልኩለዋል። ተሾመ ግራ ገባው። እምቢ ቢል ተማሪዎቹን ማሳዘን ሆነ። እሺ ቢል መንግስት ጥርስ ውስጥ ሊገባ ነው። የጸጥታ ኃላፊውን ጠየቀው። የተማሪዎቹ ጥያቄ እንደማይቆም ያወቀው ኃላፊ ዝፈን አለው፤ ዘፈነ። ያቺ ዘፈን ግን የተሾመን የሕይወት መስመር የምትቀይር ሆነች።

ከዚያ በኋላ የመንግስት የጸጥታ ሀይሎች እነ ተሾመን መከታተል እና ማዋከቡን ስራ አድርገው ያዙት። ክስ እና ምርመራ ተደጋጋሚ ሆነ። እንዲያውም በአንድ ወቅት 350 ሺ ብር ታክስ መክፈል እንዳለበት ተነገረው። ሌላ ቀን ደግሞ ዙላ ክለብ የሙዚቃ ዝግጅቱን ሊያቀርብ ዝግጅት ላይ እያለ ያለ ምንም ምክንያት ታሰሮ የዝግጅቱ ቀን ካለፈ በኋላ በዋስ ተለቀቀ።

ይህ ነገር ከቀጠለ ለሕይወቱም እንደሚያሰጋው ያወቀው ተሾመ ከአገር ለመውጣት ወሰነ። የዴንማርክ እና የስዊድን ቪዛ ነበረውና ወደ ኮፐንሀገን ከዚያም ወደ ስዊድን ሄደ። ኮፐንሀገን እንደደረሰ ከአውሮፕላን ወርዶ ታክሲ ሲሳፈር የመጀመሪያ ጥያቄው ሙዚቃ ወዳለበት ቦታ ውሰደኝ የሚል ነበር። ሹፌሩ ወደ አንድ ፐብ ወሰደው። ሆቴል ገብቶ ልብሱን ከቀየረ እና ጥቂት እረፍት ካደረገ በኋላ ወደ ቡና ቤቱ ተመለሰ። ጥብስ አዘዘ ፤ ውስኪም ተጎነጨ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ባንዱ ሙዚቃ ጀመረ። የባንዱን መሪ ጠርቶ ፒያኖ ልጫወት ሲል ጠየቀው። ሰውየው ግራ ገባው። ቆይ ባለቤቷን ላናግር አለ። ባለቤቷ ስታየው ተሾመ ከነስታት ወገን መሰላት። በእርግጥም በወቅቱ ኮፐንሀገን ላይ እንኳን የጣልያን ሱፍ ለብሶ የተጠበሰ ስጋ ከውስኪ ጋር የሚመገብ ቀርቶ መደበኛው ጥቁርም ብዙ አይታይም ነበርና ነው የገረማት። ፈቀደችለት። ተጫወተ። ወደደችው። ከባንዱ ጋር እንዲሰራ ጠየቀችው። ተስማማ ፤ ሰራ።

ከሶስት ወር በኋላ ግን ለሙዚቃ ትምህርት ከኮፐንሀገን ይልቅ ስዊድን እንደምትሻል ሰማና ወደ ስዊድን ተሻገረ። ስዊድን ከሙዚቀኝነቱ ይልቅ የአባቱ ምኞት የነበረውን ትምህርት ብዙ የገፋበት አገር ናት። ለበርካታ አመታት በዚያ ከቆየ በኋላ ወንድሙን ሊጎበኝ ወደ አሜሪካ ሄደ። እዚያ ደግሞ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ሲያይ ደስ አለው። ስለዚህም ቀጣይ ኑሮው አሜሪካ መሆን እንዳለበት ወሰነ። አሁንም እዚያው ነው የሚኖረው።

ተሾመ የራሱን ሙዚቃዎች አብዛኛውን ራሱ የጻፋቸው ናቸው። መመሰጥ እና ጊዜ ወስዶ ማሰላሰል ይወዳል። እንዲያውም እናቱ እንዲህ ቁጭ ብሎ ሲያሰላስል ሀዘን የገባው ይመስላቸውና ምን ሆንክ ምን እየሰራህ ነው ብለው ይጠይቁታል። ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት ይሰራበት ከነበረበት ክለብ ባለቤቶች ጋር አለመስማማት ተፈጥሮ ቤት ቁጭ ብሎ በሚያሰላስልበት ወቅት ይህንኑ ጥያቄ ጠይቀውት እያሰብኩ ነው ሲላቸው «አይዞህ ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል» ብለው አጽናንተውታል።

ለእናቱ የተሾመ የሀሳብ ምንጭ ስራ አጥነቱ የመሰላቸው ቢሆንም ተሾመ ግን የሚያስበው ሀሳብ ሙዚቃን እና ለሙዚቃ የሚሆነውን ሀሳብ ብቻ ነው። ዛሬም ድረስ የምንወዳቸው ሙዚቃዎቹ የተገኙትም በዚህ መሰል ተመስጦ ነው። በዚህ የሀሳብ መንገድ ከተፈጠሩት ሙዚቃዎች መሀከል አንዱ «ጋራ ስር ነው ቤትሽ» ተሾመ ስራ በፈታበት ሰሞን የሚኖርበትን ሰፈር በደንብ ካስተዋለ በኋላ የደረሰው ሙዚቃ ነው። ሙዚቃውን መጀመሪያ ሲደርሰው ቀበና ስር ነው ቤትሽ በሚል ርእስ ነበር። የነተሾመ ሰፈር (ቀበና) ከራስጌ ኮረብታ ያለው ሲሆን ፣ ከስር ደግሞ የቀበና ወንዝ ይፈስበታል። ሙዚቃውም የተሰራው በዚህ መልክአ ምድራዊ እይታ ቀስቃሽነት ነው።

የተሾመ ሙዚቃዎች ዛሬም በአዲሱ ትውልድ እንደ አዲስ የሚዘፈኑ ናቸው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአዲሱ ትውልድ አካል የሆነችው ልጁ ኤሚሊያ ተሾመም ታዋቂ ድምጻዊ ናት። ብዙዎች በአንድ ወቅት ከፍተኛ ተደማጭነት አግኝቶ በነበረው ቢግ ቢግ ወርልድ በተሰኘ ሙዚቃዋ ያውቋታል። በአንድ ወቅት ወደ አገር ቤት መጥታ አያቷን /የተሾመን እናት/ ጎብኝታ ለአባቷ የተወለደበትን ቤት ፎቶ ይዛለት ሄዳለች።

ከሚወድህ ሕዝብ ከተለየህ በኋላ ግማሽ ሰው ነህ የሚለው ተሾመ ኢትዮጵያ አሁንም ልቡ ውስጥ ናት። የአገሩን ናፍቆት የሚወጣው በእኩለ ሌሊት ተነስቶ ፒያኖ በመጫወት እንደሆነም ይገልጻል። በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ እድገት አስተዋጽኦ ያደረጉ ጠቢባንን እውቅና በሰጡበት ወቅት በሙዚቃው ዘርፍ እውቅና ከሰጧቸው ድምጻውያን መካከልም ተሾመ አንዱ ነው።

ዓለም አቀፍ

የደቡብ አፍሪካው ፕሬዚዳንት ራማፎሳ በጎርፍ ለተጎዱ ሰዎች ፀሎት እንዲደረግ ጥሪ አቀረቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የደቡብ አፍሪካው ፕሬዚዳንት ሲሪል ራማፎሳ በአገሪቱ በጎርፍ ለተጎዱ ሰዎች ጸሎት እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል።

በደቡብ አፍሪካ የጎርፍ አደጋ 41 ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሱ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በደቡብ ምስራቅ የባህር ጠረፍ ከተማ በሆነችው ደርባን እና አካባቢው ላይ የደረሰው የጎርፍ አደጋ የበርካቶች ሕይወት የቀጠፈ አሳዛኝ ክስተት እንደነበር የሚታወስ ነው።

የአገሪቱ የነፍስ አድን ሰራተኞች ፍለጋውን በማስፋት ላይ ሲሆን ፤ እስካሁን የሞቱት ሰዎች ቁጥር ወደ 400 ገደማ መድረሱን እና ከዚህም እንደሚበልጥ ሲጂቲኤን ዘግቧል።

በዚህም የጎርፍ አደጋው "በአገራችን ከዚህ ቀደም አይተነው የማናውቀውና ብዙ ሰዎች የሞቱበት ከፍተኛ መጠን ያለው አደጋ ነው" ያሉት ፕሬዝዳንቱ፤ በደቡብ አፍሪካውያን ለተጐጂዎች እንዲጸልዩ ጥሪ አቅርቧል።

"በኩዋዙሉ-ናታል (አውራጃ) ላሉ ወገኖቻችን አስፈላጊውን ፈውስ እንዲያገኙና ሕይወታቸው እንዲቀጥል እንጸልይላቸው" ሲሉም በምስራቅ ኤርሜሎ ከተማ ላሉ የኤል-ሻዳይ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ጠይቋል።

ህጻናትን ጨምሮ 10 አባላትን ያጣ ቤተሰብ መጎብኘታቸውን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ ፤ በተፈጠረው ሁኔታ እጅጉን ማዘናቸውም ገልጿል።

"በሕይወቴ እንዲሁም በፕሬዚዳንትነት ዘመኔ ካጋጠሙኝ አሳዛኝ ጊዜያት አንዱ ነው" ሲሉ ፕሬዝዳንቱ በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ባስተላለፉት መልእክት ተደምጠዋል።

የተጎጂዎች ዘመዶች ያጋጠማቸው ስቃይ ለዓመታት የሚቆይ ሊሆን እንደሚችል ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ሁሉም ከጎናቸው ሊቆም እንደሚገባም ጥሪ አቅርበዋል።

በደቡብ አፍሪካ ያጋጠመው የጎርፍ አደጋ፤ 41 ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሱ ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጨምሮ የተለያዩ አገራት መሪዎች አደጋውን ተከትሎ ሀዘናቸውን በመግለጽ ላይ ናቸው።

ጥገኝነት ጠያቂዎችን ከዩኬ ወደ ሩዋንዳ መላክ ዓለም አቀፍ ሕግን እንደሚጻረር ተመድ ገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽን (ዩኤንኤችሲአር) ጥገኝነት ጠያቂዎችን ከዩናይትድ ኪንግደም ወደ ሩዋንዳ መላክ ዓለም አቀፍ ሕግን እንደሚጻረር ገለጸ።

"የጥገኝነት ጠያቂዎችን ጉዳይ የመመልከት ኃላፊነትን ወደ ሌላ አገር ማዘዋወር ተቀባይነት የለውም" ብሏል።

የዩኬው ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን በበኩላቸው ዕቅዳቸው ዓለም አቀፍ ሕግን እንደማይጥስ ተናግረዋል። የዩኬ የአገር ውስጥ ጉዳይ ውሳኔውን በተመለከተ በተለይም ከወጪ ጋር በተያያዘ ጥያቄዎች ቢኖሩትም ፖሊስ ሊቀረጽ እንደሆነ ተገልጿል።

ለአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሯ ፕሪቲ ፔታል የቀረቡ የቢቢሲ ምንጭ "ወደ አገሪቷ በሕገ ወጥ መንገድ የሚገቡ ሰዎችን መቀነስ ወጪ ይቀንሳል" ብለዋል።

ዩኬ ለዚህ ዕቅድ የመደበችው 120 ሚሊዮን ፓውንድ ነው።

ከጥር 1 ጀምሮ ወደ ዩኬ በሕገ ወጥ መንገድ ገብተዋል የተባሉ ሰዎች ወደ ሩዋንዳ የሚላኩበት አሠራር ነው። ሩዋንዳ ሆነው የጥገኝነት ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ ዩኬ ወስናለች።

ወደ ሩዋንዳ የሚወሰዱት የመጀመሪያዎቹ ጥገኝነት ጠያቂዎች ከሳምንታት በኋላ በረራ እንደሚኖራቸው ተገልጿል።

በመጀመሪያ የሚላኩት በአነስተኛ ጀልባ ወደ ዩኬ የገቡ ያላገቡ ወንዶች ናቸው።

ከ160 በላይ የተራድኦ ድርጅቶች እና የመብት ተሟጋቾች ዩኬ ውሳኔውን እንድትቀለብስ ጠይቀዋል። ተቃዋሚ ፖለቲከኞች እና ወግ አጥባቂዎችም የዩኬን ውሳኔ ኮንነዋል።

የዩኤንኤችሲአር ተባባሪ ዋና ጸሐፊ ጂሊያን ትሪግስ፣ የጥገኝነት ጠያቂዎችን ጉዳይ የመመልከት ኃላፊነትን ወደ ሌላ ወገን ማስተላለፍ ተገቢ አይደለም ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ቀድሞ የአውስትራሊያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ፕሬዝዳንት የነበሩት ጂሊያን፣ የጥገኝነት ጠያቂዎችን ጉዳይ ለመመልከት ከዚህ የተሻለ መንገድ አለ ብለዋል። አውስትራሊያ እአአ ከ2001 ጀምሮ የጥገኝነት ጠያቂዎችን ጉዳይ እስከምትመረምር ከከተማ ውጭ የማቆየት አሠራር ዘርግታለች። ማቆያዎች ከደረጃ በታች ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ አሠራሩን የተባበሩት መንግሥታት እና የመብት ተሟጋች ድርጅቶችም ኮንነውታል።

አውስትራሊያ ለዚህ አሠራር 811 ሚሊዮን ዶላር ከ2021 እስከ 2022 አውጥታለች።

ከዚህ ቀደም እስራኤል ኤርትራውያን እና ሱዳናውያን ስደተኞችን ወደ ሩዋንዳ ለመላክ አስባ እንደነበር የገለጹት ጂሊያን "ከአገሪቱ ወጥተው ሂደቱን በድጋሚ ለመጀመር ተገደዋል። ይህም አካሄዱ ለረዥም ጊዜ እንደማይሆን ማሳያ ነው" ብለዋል።

በርካታ የሕግ ባለሙያዎች የዩኬ ዕቅድ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጥሰትን ጨምሮ የተለያዩ ከሕግ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንደሚጠብቁት እያስጠነቀቁ ነው። በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ጥገኝነት ጠያቂዎችን አደጋ ሊደርስባቸው ወደሚችልበት አገር መላክ ክልክል ነው። አምና ዩኬ በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ ባደረገችው ንግግር በሩዋንዳ "ከሕግ ውጭ የሆነ ግድያ፣ የሰዎች መሰወር፣ እንግልት እንዲሁም የፖለቲካ እና ሲቪል መብት እጦት ያሳስበኛል" ማለቷ አይዘነጋም።

ሆኖም ግን የዩኬ የፍትሕና ስደት ሚኒስትር ቶም ፕርስግሎቭ ሩዋንዳ ባለፉት 30 ዓመታት ለውጥ እየታየባት እንደመጣና ተራማጅ አገር እንደሆነችም ይናገራሉ። ዩኬ በአነስተኛ ጀልባ ወደ አገሯ የሚገቡ ስደተኞችን ቁጥር የመቀነስ ዕቅድ አላት። ጥገኝነት ጠያቂዎችን ወደ ሩዋንዳ የመላክ ሐሳብም የዚህ አካል ነው። ይህ ዕቅድ ይፋ በተደረገበት ቀን በ14 ጀልባዎች 562 ሰዎች ወደ ዩኬ ጉዞ አድርገዋል።

አምና 28,526 ሰዎች ባሕር አቋርጠው ገብተዋል።

የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

የአመልካች ስም እና አድራሻ: ፒፒሲ ኢንተርናሽናል ሆልዲንግስ (ፕሮፕራይተሪ) ሊሚትድ (PPC International Holdings (Proprietay) Limited) አድራሻ: PPC Building, 148 Katherine Street, (Cnr Grayston Drive), Sandton, Gauteng 2146, South Africa.

የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ፡ የቃል

	ማመልከቻ ገቢ የሆነበት ቀን	የማመልከቻ ቁጥር
PPC READYMIX	30/12/2015	FTM/6982/2015

የቀለም ዓይነት፡ ጥቁር እና ነጭ

ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 19

ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች

ምድብ 19፡- የግንባታ እቃዎች (ብረት ያልሆኑ); ለግንባታ የብረት ያልሆኑ ጠንካራ ቧንቧዎች; አስፋልት, ፒች እና ሬንጅ; ሲሚንቶ; ጥራጥሬ እና የዱቄት ጥፍጥፍ, የኖራ እና የኖራ ድንጋይ; ኮንክሪት; ማያያዣዎች; በዚህ ክፍል ውስጥ የማጣበቂያ ቁሳቁስ; አሸዋ; ፕላስተር; የብረት ያልሆኑ ማጓጓዣ ሕንፃዎች; የብረት ሳይሆን የመታሰቢያ ሐውልቶች; በዚህ ክፍል ውስጥ ከተጠቀሱት ቁሳቁሶች የተሠሩ እቃዎች፡፡

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃውሞ ያለው ሰው የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ካላቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ባለቤቱ ሳይፈቅድ በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክቱን ቢገለገል ወይም ባለቤቱ በንግድ ምልክቱ ላይ ያለውን ማንኛውም ዓይነት መብቱን የሚጋፋ ተግባር ሲፈጽም ቢገኝ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ክስ እንደሚመሰረትበት እናሳውቃለን፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-219 -09/08/2014 (17/04/2022)

በድጋሚ የወጣ የግንባታ ስራ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

የደ/ብርሃን ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት የግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ቡድን በከተማ አስተዳደሩ በጀት፤

1. ሎት 02 ቀበሌ 09 የቢሮ ጥገና ስራ በፓኬጅ ቁጥር D/Berhan/M-07/2021/22

ደረጃ 7 እና በላይ የሆኑ በጠቅላላ ስራ ተቋራጭ/GC/ ወይም በህንፃ ስራ ተቋራጭ /BC/ የሆኑ ስራ ተቋራጮችን በድጋሚ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በዘርፉ ፈቃድ ያላቸው እና የታደሰ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተወዳዳሪዎች በጨረታው መሳተፍ ይችላሉ፡፡

1. በ2014 በጀት ዓመት የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው፣
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /Tin Number/ ያላቸው፣
3. የግዥ መጠኑ ከብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ እና በላይ ከሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
4. ተጫራቾች ከአማራ ክልል ውጭ የንግድ ፈቃድ ያላቸው ከሆነ የታደሰ የፌደራል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከተራ ቁጥር 1-4 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻው ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች የመጫረቻ ዋጋቸውን መ/ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. የግንባታዎቹን የስራ ዝርዝር መግለጫ /Specification/ እና መወዳደሪያ መስፈርቶቹን ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይችላሉ፣
8. በጨረታው ሰነድ ላይ ስርዝ ድልዝ ወይንም ለመለየት አሻሚ የሆነ ፅሁፍ መኖር የለበትም፣
9. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ ቡድን 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመምጣት ለእያንዳንዱ ጨረታ የማይመለስ ብር 100/አንድ መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ገዝተው መጫረት ይችላሉ፡፡
10. ተጫራቾች ለ30 ተከታታይ ቀናት ፀንቶ የሚቆይ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /ቢድ ቦንድ/ ብር 42,680/አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ ሲ.ፒ.ኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና/ጋራንቲ/ በስማቸው ለደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት በሚል አድራሻ ከኦሪጅናል ሰነዱ ጋር አብሮ ማቅረብ አለባቸው፡፡
11. ማንኛውም ተጫራች ለሚወዳደርበት የግንባታ ጨረታ ህጋዊ ማስረጃዎቹን እና የጨረታ ሰነዱን በአንድ ላይ በማድረግ በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ በደ/ብርሃን ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት ግ/ፋ/ን/አስ/ቡድን 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 12 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በስራ ሰዓት ማስታወቂያው በጋዜጣ በድጋሚ ግልፅ ጨረታ ከወጣበት እለት ጀምሮ ለ21 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
12. ጨረታው በጋዜጣ በድጋሚ ግልፅ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ22ኛው ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በደ/ብ/ከ/አስ/ከ/ል/ቤ/ኮ/አገ/ጽ/ቤት ግ/ፋ/ን/አስ/ቡድን 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 12 በ4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል ፡፡ ዕለቱ ቅዳሜ፣ እሁድ ወይም የህዝብ በዓላት ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ እለት 4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በራሳቸው ምክንያት ባይገኙ የጨረታው ፖስታ ተሟልቶ ከተገኘ እንዲከፈት በማድረግ ውድድሩ ይካሄዳል፡፡
13. አሸናፊው ተጫራች ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ከ5 የስራ ቀን በኋላ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የሚፈለጉበትን ማስረጃዎች በማቅረብ ውለታ መፈፀም ይኖርበታል፡፡
14. በጨረታው አሸናፊ የሆነ የውል ማስከበሪያ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ 10 በመቶ /10%/ በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ/ሲ.ፒ.ኦ./CPO/ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማስያዝ ይኖርበታል፡፡
15. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ወይም አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት አለው፣
16. በማስታወቂያው ያልተገለፁ ነገሮች ቢኖሩም በግዥ መመሪያው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
17. ተጫራቾች ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

በደ/ብርሃን ከተማ አስተዳደር የከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽንና አገልግሎት ጽ/ቤት

ሁለንተናዊ የስብእና ትምህርት ለልጆች

አስናቀ ፀጋዬ

ልጆች እንዴት ናችሁ፡፡ ትምህርትስ እንዴት ነው። እየተማራችሁ ነው? በደንብ እያጠናችሁ ነው? ጎበዞች! በደንብ ካጠናችሁ ጥሩ ውጤት ታመጣላችሁ፡፡ ጥሩ ውጤት ያመጣ ተማሪ ደግሞ ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ይሸጋገራል፡፡

ልጆች ለመሆኑ በትምህርት ቤት ከምታገኙት እውቀት በተጨማሪ ከወላጆቻችሁ የምታገኙት እውቀትና ምክር ለወደፊት ሕይወታችሁ መቃናት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለውስ ታውቃላችሁ? አዎ! ወላጆቻችሁ ከትምህርት ቤት መምህሮቻችሁ ባልተናነሰ ያላቸውን ልምድና እውቀት ለእናንተ በማካፈል ተጨማሪ እውቀት እንድታገኙ ያግዟችኋል፡፡ በተለይ ደግሞ የተሟላ ሰብእናን ተላብሳችሁና በመልካም ስነ ምግባር ታንጻችሁ እንድታድጉ የወላጆቻችሁ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡

ታዲያ ወላጆቻችሁ እናንተ ልጆቻችው በመልካም ስነ-ምግባር፣ ስብእናና ስነልቦና ታንፃችሁ እንድታድጉ የሚያደርጉት አንድም ከሃይማኖታቸው በቀሰሙት ትምህርት ሁለትም ከሕይወት ልምዳቸው ወይም ፈጣሪያቸው ከሰጣቸው ፀጋ በመነሳት ነው። አንዳንድ ወላጆች ደግሞ የተማሩ ከሆኑ በሕይወት ዘመናቸው ያካባቱትን እውቀት ተጠቅመው እናንተን ይቀርፃሉ፡፡

ልጆች! እናንተ ሙሉ ስብእና እንዲኖራችሁና እድገታችሁም የተሟላ እንዲሆን ብሎም ሙሉ ችሎታችሁን እንድትጠቀሙበት ገና ከፅንስ ጀምሮ እርዳታውና ክትትሉ ያስፈልጋችኋል፡፡ የዚህ እድገት ወሳኞቹና ትልቁን አስተዋፅኦ የሚያደርጉት ደግሞ ወላጆቻችሁ፣ አሳዳጊዎቻችሁና ከእናንተ ጋር ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉ ሰዎች ናቸው፡፡

ሆኖም በአሁኑ ጊዜ የአኗኗር ዘይቤውና ሕይወት እየተቀየረ በመምጣቱና ዓለም ወደ ዲጂታል ዘመን እየተቀየረች በመምጣቷ ወላጆቻችሁ ከዚህ ጋር በሚሄዱ ክሂሎቶች ራሳቸውን ማብቃት ይኖርባቸዋል፡፡ እናንተ የተሟላ ስብእና ይዛችሁ እንድታድጉ በልጆቻቸው አስተዳደግ ዙሪያ ተጨማሪ እውቀት ያስፈልጋቸዋል፡፡

ዊዝኪድስ ዎርክሾፕ ሶሻል ኢንተርፕርይዝ የተሰኘውና «ፀሐይ መማር ትወዳለች» በሚለው የቴሌቪዥን ፕሮግራም የሚታወቀው ድርጅት ደግሞ በቅርቡ ወላጆች በኢንተርኔት አማካኝነት በልጆቻቸው ስብእና ግንባታ ዙሪያ የተለያዩ ትምህርቶችን የሚቀስሙበትን መንገድ አመቻችቷል።

ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር በተለይ ደግሞ ከአእምሮ ሊሂቃኖች፣ ከስነ ልቦና ባለሙያዎች፣ ከመምህራን ጋር በመሆን ለወላጆች በጥናት ላይ የተመረኮዙ ኮርሶች በኢንተርኔት አማካኝነት ይሰጣል፡፡ ወላጆችም በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የልጆቻቸውን በራስ መተማመንና የስሜት ክሂሎት ለማሳደግ የሚያስችሏቸውን ክሂሎቶች ያገኙበታል፡፡

በዋናነት ፕሮግራሙ ደግሞ ወላጆች ልጆቻቸው በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች ምን አይነት ስሜቶችን እንደሚያሳዩ፣ እንዴትስ እነሱን መርዳት እንደሚችሉ፣ ምን አይነት ስነ ልቦና እንዳላቸውና ይህንንም እንዴት ማበልፀግ እንደሚችሉ፣ ምን አይነት አካላዊ እድገት እንደሚያመጡና ከነዚሁ ጋር በተያያዙ ያሉ መረጃዎችን በህፃናት ሀኪሞች፣ የስነ ልቦና ባለሙያዎችና የአእምሮ ሀኪሞች አማካኝነት በአጭሩ የሚያገኙበት ነው፡፡

እናንተም ልጆች ወላጆቻችሁ የወላጅነት ትምህርት ፕሮግራሙን ለመከታተል እንዲችሉ በቅድሚያ http://www.t4f.et በተሰኘው የድርጅቱ ድረ ገፅ ውስጥ ገብተው

እንዲመዘገቡ ንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም የመረጡትን የልጆች ስብእና ለመገንባት የሚያስችላቸውን ነፃ የክሂሎት ኮርሶችን መከታተል እንደሚችሉ ይጠቁ ሟቸው። ከ200 ብር ጀምሮ በመክፈል መከታተል የሚፈልጓቸው የሕይወት ክሂሎት ኮርሶችም በድረ-ገፁ ላይ እንደሚያገኙ ግለፁላቸው፡፡

ይህን ካደረጋችሁ ልጆች ወላጆቻችሁ በሁለንተናዊ የልጆች ስብእና ግንባታ ዙሪያ የተሟላ ክሂሎት ስለሚኖራቸው እናንተን በዚህ መንገድ ቀርፆ ለማሳደግ አይቸገሩም፡፡ እናንተም በመልካም ስብእናና ስነ ምግባር ታንፃችሁ በማደግ አገራችሁ ኢትዮጵያን ወደ ተሻለ ነገ ታሻግራላችሁ፡፡ መልካም እለተ ሰንበት!!

ስፖርት

ለምርጥ የረጅም ርቀት አትሌትነት

ብርሃን ፈይሳ

በስፖርቱ ዓለም እጅግ አስደናቂ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ረጅም ርቀትን በሩጫ የመሸፈን ብቃት ነው፡፡ በተለይ 42 ኪሎ ሜትሮችን የሚሸፍነው ማራቶን ከፍተኛ ጽናትና በልምምድ የዳበረ ጥንካሬን ስለመጠየቁ እርግጥ ነው፡፡ ነገር ግን ብዙዎች ይህንን ፈታኝ ውድድር በተደጋጋሚ ከማሸነፍ ባለፈ የሚገቡበትን ሰዓት በማሻሻል ሳይንስ ሊተነብየው ከሚችለውም በላይ የሰው ልጅ እምቅ አቅም ምን ድረስ እንደሆነ ማሳያ እስከመሆን ደርሰዋል፡፡

የስፖርት ባለሙያዎችም ከዚህ በመነሳት እንዲሁም እጅግ ፈታኝ በሆነው ይህንን ውድድር አሸንፈው ስኬታማ ለመባል የቻሉበትን ምስጢር ለማወቅ ተደጋጋሚ ጥናቶችን አድርገዋል፡፡ በዚህም ሌላኛውን አስደናቂ ውጤት ያገኙ ሲሆን፤ ይኸውም በውድድር አሸናፊ ሊሆኑ የቻሉት ምናልባትም በውድድር ከሚሸፍኑት ርቀት በርካታ እጥፍ የሚሆኑ ኪሎ ሜትሮችን በልምምድ ወቅት በመሮጣቸው ሊሆን ይችላል የሚል ነው፡፡

«ስፖርትስ ሜድስን» የተባለው ጆርናል ያወጣው ጥናት እንደሚያመላክተው ከሆነም የማራቶን አትሌቶች በሳምንት በአማካይ ከ160 እስከ 220 ኪሎ ሜትር በልምምድ ወቅት ይሸፍናሉ፡፡ የመም ረጅም ርቀት እንዲሁም የጎዳና 5 እና 10 ኪሎ ሜትር ሯጮች ደግሞ በአማካይ በሳምንት ውስጥ ከ 130–190 ኪሎ ሜትር የሚሆን ርቀት በመሮጥ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡

ይህንን ከባድ ልምምድ ለመስራትም ሆነ

በውድድሮች ላይ ውጤታማ ለመሆንም አትሌቶችም ሆኑ አሰልጣኞቻቸው በቅድሚያ የስልጠና እና የውድድር መርሃ ግብርን ማዘጋጀት የግድ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ከ59 የሚሆኑ ታዋቂ የጎዳና ላይ አትሌቶች እና 16 አሰልጣኞች በተሰበሰበው ናሙና በተጠናቀረው ጥናት መሰረት የአትሌቶችና አሰልጣኞቻቸው ቀዳሚ ስራ የስልጠና መርሃ ግብር ማውጣት እንዲሁም በዓመቱ መጀመሪያ በየትኛዎቹ ውድድሮች መሳተፍ እንደሚፈልጉ ለይተው እቅድ ማውጣት ነው፡፡ ይህ የልምምድ መርሃ ግብር እረፍትንም የሚያካትት ይሆናል፡፡

የመም ረጅም ርቀት አትሌቶች በዓመት ውስጥ ተደጋጋሚ ውድድሮች ላይ ተሳታፊ እንደመሆኑ የልምምድና የእረፍት ጊዜያቸውም በዛው ልክ የታቀደ እና አጭር የጊዜ ገደብን ያካተተ ይሆናል፡፡ የጎዳና በተለይ የማራቶን ሯጮች ግን ከመም አትሌቶች በተለየ መልኩ የልምምድም ሆነ የእረፍት ጊዜ ብቻም ሳይሆን የውድድር ተሳትፎ ሂደት ይኖራቸዋል፡፡

አንድ አትሌት በዓመት ውስጥ ከሁለት እስከ ስድስት ውድድሮች ላይ ብቻ የሚሳተፍ ሲሆን፤ በውድድሮቹ መካከል ደግሞ እስከ ሶስት ወራት የሚደርስ የእረፍት ጊዜ ሊኖረው ይገባል፡፡ የልምምድ ሁኔታውም የተለየ ሲሆን የረጅም ርቀት አትሌቶች በውድድር ወቅት ከሚሮጡበት ፍጥነት ባነሰ(እስከ 80 በመቶ የቀነሰ) መልኩ ለልምምድ የተያዘላቸውን ርቀት እንዲያጠናቅቁ ይመከራል፡፡ ይኸውም ከሶስት እስከ አምስት የሚሆነውን ርቀት በአንድ ሰዓት ውስጥ መሮጥ ሲሆን፤ ምርጥ አሰልጣኞች ይህንን በማመጣጠን በምን ሁኔታ ወደፊት መስፈንጠር ይቻላል የሚለውን በሚገባ ያሳያሉ፡፡

በልምምድ ወቅት አካላዊ ስሜትን ማዳመጥና መቆጣጠርም መሰረታዊ ነገር መሆኑን ከአትሌቶቹ የተገኘውን መረጃ ዋቢ በማድረግ ጥናቱ ያመላክታል። ልምምዱን ተከትሎ በውስጣዊ የአካል ክፍሎችም ሆነ በውጫዊ አካላት ጫና መፈጠር አለመፈጠሩን መለየትና ከተቻለም መዝግቦ በማስቀመጥ ምን መስራት ይገባል እንዲሁም የትኞቹ መቀነስ አለባቸው የሚለውን ማወቅ ይቻላል፡፡ ይህም ስልጠናው በሳይንሳዊ መንገድ እንዲመራ እና ወደ ውጤታማነት መራመድ እንዲቻል ምቹ መደላደልን ይፈጥራል፡፡ ስልጠናው በዚህ መልክ ከቀጠለ በኋላ ልምምድን እየቀነሱ መሄድ አስፈላጊ መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል፡፡ ከሁለት እስከ ሶስት ሳምንት ለሚሆን ጊዜ ቀድሞ ከነበረው የልምምድ አጠቃላይ ሁኔታ እና መጠን ከ40 እስከ 60 በመቶ የሚሆነውን መቀነስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ውድድሮች ለመካሄድ ከሰባት እስከ አምስት ቀናት ሲቀሩትም በተመሳሳይ መልኩ ልምምድን መቀነስ በበርካታ አትሌቶች ዘንድ የተለመደ ነው፡፡